# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 176 የካቲት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሀብት ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ ተሻገሯል

## -ኪሣራ ውስጥ የነበሩ የልማት ድርጅቶች ወደ ትርፋማነት ተሸጋግረዋል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ በማንቀሳቀስ በአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ ጉልህ ሚና እየተወጡ መሆኑን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር አስታወቀ፡፡ ቀደም ሲል በኪሣራ ውስጥ የነበሩ የልማት ድርጅቶች ወደ ትርፋማነት ተሸጋግረዋል ተብሏል፡፡

የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ሲሆን፤ ሰፊ የሆነ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአገሪቱ እምቅ የሰው ኃይል እና ቁሳዊ ሀብትንም ጭምር የያዙ ናቸው፡፡ በአሁኑ

የመንግሥት ልማት...... ወደ ገጽ 5 ዞሯል


ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ

አቶ ሐብታሙ ኃይለሚካኤል

# በተፈጠረው ሰላም የመስኖ ልማት እያካሄዱ ያሉ የትግራይ አርሶ አደሮች

**ጌትነት ምህረቴ**

ሽረ፡-ከሽረ ወደ አክሱም በሚወስደው አውራ ጎዳና 15 ኪሎ ሜትር እንደተጓዝን ባገኘነው ታይታይ ቁራሮ ወረዳ ሽንብራ፣ በቆሎ፣ ሽንኩርት፣ ጎመንና ቲማቲም በመስኖ እየለሙ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡

አርሶ አደር ፀጋይ በርሄ፤ ከዚህ ቀደም ባዘጋጁት የውሃ ማቆሪያ ጉድጓድ በውሃ መሳቢያ ሞተር ተጠቅመው

በተፈጠረው ሰላም ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ፎቶ - እዩብ ተፈራ



# የመማሪያ መጻሕፍት በወቅቱ አለመሰራጨቱ ለትምህርት ጥራት ተጨማሪ እንቅፋት ነው

ገጽ 5

# ባለ ማቀዝቀዣ ሕንፃው የምግብ ብልሽትንና የአምራቾችን ኪሳራ የሚያስቀር ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በ1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሚገነባው ዘመናዊ ባለ ማቀዝቀዣ ሕንፃ የምግብ ብልሽትንና የአምራቾችን ኪሳራ የሚያስቀር እንዲሁም የወጪ ንግድ ምርትን የሚያሳድግ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚያስገነባው ባለ10 ወለል የቅይጥ አገልግሎት የሚሰጠው ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ትናንት የመሠረት ድንጋይ ተቀምጧል፡፡

የመሠረት ድንጋዩን የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አቻ ደምሴ፣ የኮርፖሬሽኑ የቦርድ ሰብሳቢ እና የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሐሰን መሐመድ አስቀምጠዋል፡፡

ባለ ማቀዝቀዣ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ




















አቶ ጋሻው አይችሉህም

# ኮርፖሬሽኑ ዓመታዊ ሽያጩን 12 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ለማድረስ እየሠራ ነው

## - 242 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ተሰብስቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ዓመታዊ የሽያጭ መጠኑን ወደ 12 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

በ2014/15 የምርት ዘመን ኮርፖሬሽኑ ከ15 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ላይ በሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች እስከ የካቲት ወር አጋማሽ ድረስ 242 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር መሰብሰቡ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የኮሙዩኒኬሽን ኃላፊ አቶ ጋሻው አይችሉህም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ኮርፖሬሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ያከናወነው የ5 ቢሊዮን ብር የሽያጭ ገቢ በ2015 ዓ.ም ወደ 12 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ አቅዶ እየሠራ ነው፡፡

አቶ ጋሻው እንደገለጹት፤ በዓመታዊው የገቢ ሪፖርቱ መሠረት በ2014 በጀት ዓመት ከታክስ በፊት 546 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር አትርፏል። ትርፉን በ2015 ዓ.ም ወደ አንድ ቢሊዮን ብር ለማሳደግ እየሠራ ይገኛል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ለግብርና ምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርጉና ለዘመናዊ እርሻና ለአግሮ ኢንዱስትሪ መስፋፋት መሠረት የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም የግብርና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት መሆኑን አቶ ጋሻው አስታውቀዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በአሁኑ ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ ምርጥ ዘር በማቅረብ ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ በ2014 በጀት ዓመት ከ14 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በምርጥ ዘር በመሸፈን 282 ሺህ ኩንታል ምርት መሰብሰቡን አስታውሰዋል።

በ2014/15 የምርት ዘመን ኮርፖሬሽኑ 15 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በምርጥ ዘር በመሸፈን እስከ የካቲት 16 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ 242 ሺህ ኩንታል ምርት መሰብሰቡን ኃላፊው አስታውቀዋል።

ተቋሙ የ21 ሰብሎችን 70 ዓይነት ዝርያዎች በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ላይ መሆኑን አቶ ጋሻው ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ ለምርታማነት ማደግ የላቀ አስተዋጽዖ ያላቸውን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያዎችን በጠጣርና በፈሳሽ መልክ በማቅረብ ላይ መሆኑን በመግለጽ፤ የጸረ ተባይ፣ የጸረ አረምና የጸረ ነፍሳት ኬሚካሎችንና የእንስሳት መድኃኒቶችን ለሽያጭ በማቅረብ ላይ እንደሚገኝ ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በተቀናጀ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የደረሰ ሰብል በተመጣጣኝ ዋጋ በመሰብሰብና በራሱ ትራንስፖርት አጓጉዞ በማስረከብ የተሟላ አገልግሎት መስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ባሉት የአጭዶ መውቂያ መሣሪያዎች እስከ የካቲት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ 155 ሺህ ኩንታል ምርት በመሰብሰብ ለደንበኞቹ ማስረከብ መቻሉን አቶ ጋሻው ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ ለ2015/16 የሰብል ዘመን 12 ሚሊዮን 875 ሺህ 520 ኩንታል ኤንፒኤስና ዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ ከውጭ ለማስገባት እየሠራ ነው። በዚህ መሠረት እስከ የካቲት ወር አጋማሽ ድረስ ድረስ 3 ሚሊዮን 480 ሺህ 860 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ጂቡቲ ወደብ ደርሶ አብዛኛው ለአርሶ አደር ዩኒየኖች ተሰራጭቷል።

አቶ ጋሻው እንዳስታወቁት ፤ በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ ለተጠቃሚዎች በሚያቀርባቸው ምርቶች አማካኝነት ዓመታዊ ትርፉን ከ45 ነጥብ 6 ሚሊዮን ብር ወደ 1 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ አቅዶ እየሠራ ይገኛል።

# ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ለማህበረሰቡ መፍትሔ የሚያስገኙ ጉዳዮች ላይ ማተኮር አለባቸው

**ሞገስ ተስፋ**

አዳማ፡- በ2014 ዓ.ም የ12 ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች በቀጣይ ለማህበረሰቡ መፍትሔ የሚያስገኙ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ተገለጸ።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ 76 ተማሪዎች እውቅናና ሽልማት ሰጠ።

በዕውቅናና ሽልማት መድረኩ የኦሮሚያ ልማት ማህበር የቦርድ ሰብሳቢ አቶ አባዱላ ገመዳ፤ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የውጭ የትምህርት ዕድል በመጠቀም ለማህበረሰቡ መፍትሔ በማምጣት ረገድ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

ትምህርት የሁሉም ነገር ቁልፍ ነው ያሉት አቶ አባዱላ፤ ዛሬ በጥረት ለዚህ ደረጃ የደረሱ የአዳሪ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ዕውቀታቸውን በማጠናከር ኅብረተሰቡን ወደ ብልፅግና የሚያሸጋግሩበት መንገድ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቱ ሲቋቋም እንደ ክልል፣ እንደ አገር ብሎም እንደ አፍሪካ ተወዳዳሪ ዜጎችን ለማፍራት ነው። አሁን ላይ ልዩ ተሸላሚ የሆናችሁ ተማሪዎችም የአገራችሁንና የሕዝባችሁን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት የሚረዱ ሥራዎች ላይ ከወዲሁ ትኩረት ልታደርጉ ይገባል ሲሉ አቶ አባዱላ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ በበኩላቸው፤ ተማሪዎች ልክ እንደ ዶክተር አክሊሉ ለማና ሌሎች ምሁሮች ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን በመሥራት ያስተማራችሁን ማህበረሰብ ማገልገል ይጠበቅባችኋል ብለዋል። በዚህ ረገድ በጤናው፣ በኢንጂነሪንጉና በተለያዩ ዘርፎች ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባችኋል ሲሉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ኢቲቻ በበኩላቸው፤ የልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቱ በኦሮሚያ



ተማሪ ጌጤ ቦና



ተማሪ ሮቤል አስመራ

ክልል ያለውን የትምህርት ጥራት ችግር ለመፍታት የተቋቋመ ነው።

በተለይም ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ተቀብሎ በማስተማር የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል። እውቅናና ሽልማት የተሰጣቸው ተማሪዎች በቀጣይም ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ራሳቸውንና አገርን የሚለውጡ እንደሚሆኑ ሙሉ እምነት አለን ሲሉ ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ በ2014 ዓ.ም ያስፈተናቸውን 76 ተማሪዎች ያሳለፈ ሲሆን፤ 21ዱ ተማሪዎች ከ600 በላይ ሲያመጡ 45 ተማሪዎች ደግሞ ከ500 በላይ ውጤት አምጥተዋል። ቀሪዎቹ ደግሞ ከ400 በላይ አስመዝግበዋል።

ትምህርታችንን በሚገባ በመከታተል የሕዝባችንን ችግሮች መፍታት የሚያስችሉ ምርምሮችን መሥራት ህልማችን ነው ሲሉ በኦሮሚያ ልማት ማህበር ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ገልጸዋል።

637 ውጤት በማምጣት የዋንጫ ተሸላሚዋና በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ የውጭ የትምህርት ዕድል ያገኘችው ተማሪ ጌጤ ቦና እንደገለጸችው፣ በልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት እንደመማሬ ጥሩ ውጤት አስመዝግቤያለሁ። በቀጣይም የአገሬን ችግር መቅረፍ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አደርጋለሁ ብላለች።

በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 652 በማምጣት የውጭ የትምህርት ዕድል ያገኘው ተማሪ ሮቤራ አስመራ በበኩሉ፤ በቀጣይ «በሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ» ዘርፍ በመማር በቴክኖሎጂው መስክ ችግር ፈቺ ሥራዎች ለማበርከት ከወዲሁ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ለወጡ ወንድና ሴት ተማሪዎች የሜዳሊያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ የምስክር ወረቀትና የታብሌት ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።

# ከኢትዮጵያ የተወሰዱ የአቪየሽን ቅርሶችን የማስመለስ እንቅስቃሴ ተጀመረ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ጊዜያት ከኢትዮጵያ የተወሰዱ የአቪየሽን ቅርሶችን ለማስመለስ የኢትዮጵያ ሲቪል የአቪየሽንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እንቅስቃሴ መጀመራቸው ተገለፀ::

‹‹ፀሐይ የኢትዮጵያ የአቪየሽን አጀማመር›› የሚል መጽሐፍ ደራሲ የሆኑት ካፒቴን ዘላለም አንዳርጌ፤ ጥቂት አገሮች ብቻ የአውሮፕላን ባለንብረት በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ የራሷ አውሮፕላንና ፓይለት ነበራት ያሉ ሲሆን፤ ከዚያም በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን በአውሮፕላን ስሪት ላይ ጭምር ይሳተፉ ነበር ብለዋል::

ኢትዮጵያውያን ፀሐይ የምትባል የአውሮፕላን ስሪት ላይ ተሳትፈውባት እንደነበር አብራርተዋል:: በአሁኑ ወቅትም ይቺ አውሮፕላን በአውሮፓ አንድ አገር ሙዚየም ውስጥ እንደምትገኝ ነው ካፒቴን ዘላለም የገለፁት::

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማህበራዊ ጉዳዮች አማካሪ ሚኒስትር ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤ ጉዳዩ ቀላል ባይሆንም ከዚህ በፊት በቅርስ ማስመለስ ሥራ ላይ ልምዱ ያላቸውን ሰዎች አሳትፎ መሥራት ከተቻለ ኢትዮጵያ ቅርሶቿን የማታስመልስበት ምክንያት አይኖርም ብለዋል:: ለዚህም ይህንን የሚመለከት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋሞች ጋር የሚሠራ አካልን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ገልጸዋል::

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ኮሎኔል ብሩክ ሰይፉ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ታሪክ አቪየሽን ኢንዱስትሪ በቀዳሚነት



ሰፋፊ ክንውኖችን ያሳለፈች ስትሆን ይህም ለበርካቶች በኩራትና በማስተማሪያነት የሚነሳ ነው:: በ1920ዎቹም በአቪየሽን ውስጥ በቀዳሚነት ስትሳተፍ የነበረች አገር ስትሆን በዚህ መነሻነት በአሁኑ ወቅትም በዘርፉ ሥመ ገናና ከሆኑ በአፍሪካና በዓለም አገራት ተርታ የምትመደብ ናት:: በመሆኑም የአቪየሽን ታሪካዊ ቅርሶችን ለመመለስ የተጀመረው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን ጠቁመው፤ የሚመለከታቸው አካላት ታሪካዊ ፍልሚያ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: የኢትዮጵያ አየር ኃይልም ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ አረጋግጠዋል::

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው መንግሥቴ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአቪየሽን ታሪክ በዓለም ላይ ቀዳሚ ከሚሰኙ አገራት ተርታ የምትመደብ ስትሆን ለአፍሪካ አገራት ደግሞ እርሾ ነበረች ብለዋል:: በእነዚህ ዘመናት ውስጥም ታሪካዊ የሚባሉ ክንውኖች እንደነበሩ አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ በራሷ አቅም አውሮፕላን እስከመገጣጠም የደረሰች መሆኗን አስገንዝበዋል:: ይሁንና በታሪክ አጋጣሚ መሰል ቅርሶቿ ተወስደውባታል:: በመሆኑም እነዚህን ቅርሶች ካለበት ቦታ በመፈለግ ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ጥረት መጀመሩን አስገንዝበዋል::

እንደ አቶ ጌታቸው ገለፃ፤ ታሪካዊ የአቪየሽን ቅርሶችን ለመመለስ የሚደረገው ጥረት የበርካታ አካላትን ጥረት እንደሚጠይቅ ጠቁመው፣ በዚያው ልክ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም መንግሥትም ሆነ ስለታሪኩ ግንዛቤው ያላቸው አካላት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ጠይቀዋል::

ቀደም ሲል የአክሱም ሐውልትን ጨምሮ በርካታ መንፈሳዊና ዓለማዊ ቅርሶች ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ማስመለሷ ይታወቃል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የድርቅ አደጋን መቋቋም የሚችል አካባቢያዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት!

የምሥራቅ አፍሪካ አገራት ለአየር ንብረት ለውጥ በብዙ መንገድ የተጋለጡ ናቸው። ይህ የአደጋ ተጋላጭነታቸው በተለያዩ ወቅቶች ለከፋ የድርቅ አደጋ ዳርጓቸዋል። በአደጋዎቹም ከፍተኛ ለሆኑ ሰብአዊና ቁሳዊ ችግሮች ተዳርገዋል።

አገራቱ ካላቸው ዓለም አቀፍ ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አንጻር የብዙዎች ዓይን ማረፊያ ከመሆናቸው በላይ ያለመረጋጋትና የግጭት ምንጭ ናቸው፤ ይህና ሌሎችም ተግዳሮቶች ተደማምረው የደካማ ኢኮኖሚ ባለቤት አድርጓቸዋል፤ አደጋ የመቋቋም አቅማቸውን በእጅጉ ተፈታትኖታል። ዛሬም እየተፈታተነው ይገኛል።

ከዚህ ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከሰተ ያለው የአካባቢ የአየር ብክለት በአግባቡ ካልተያዘ ለአካባቢ አገራት ሕዝቦች «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» በመሆን፤ ያልዘሩትን እንዲያጭዱ ተጨማሪ የከፋ እርግማን ሆኖ ሊከሰት እንደሚችል ይጠበቃል።

ይህንንም በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጮኹ ድምፆች እየተበራከቱ ቢሆኑም፤ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በተለይም የችግሩ ዋነኛ ምክንያት የሆኑት አገራት ለድምጾቹ ጆሮ የመንፈጋቸው እውነታ አገራቱ በቀጣይም በተመሳሳይ አደጋ /በከፋ መልኩ ሰለባ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመላካች ነው።

አሁን ላይም ቢሆን ከተከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ በአምስት ተከታታይ የዝናብ ወቅቶች ዝናብ ባለመጣሉ ምክንያት የአካባቢው አገራት በሆኑት በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በሶማሊያ 31.6 ሚሊዮን ሰዎች ለድርቅ አደጋ ተጋላጭ ሆነዋል።

ድርቁ በተለይም በአገራቱ የሚኖሩ የአርብቶ አደር ማኅበረሰቦችን ለረሃብ፤ የሕይወታቸው መሠረት የሆኑ የቤት እንስሳትን ለእልቂት እየዳረገ መሆኑ፤ የማኅበረሰቡን ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገዎቹንም ጭምር ጽልመት እያለበሰው ነው።

በርግጥ የአካባቢው አገራት ያላቸውን ሰፊ የተፈጥሮ እና የሰው ሀብት በአግባቡ ማልማት የሚያስችል የተረጋጋ የፖለቲካ ምህዳር ቢኖራቸው፤ አገራዊ የመልማት አቅማቸው በወቅቱ ብዙ ዋጋ እያስከፈላቸው ያለውን የድርቅ አደጋ ከመታደግ ባለፈ ነገዎቻቸውን ብሩህ ማድረግ የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም እንዳለው ይታመናል።

አገራቱ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የጋራ መሆኑን ተገንዝበው፤ በመካከላቸው ያለውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነቶች በማጠናከር፤ በመተማመንና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት በመፍጠር የመልማት አቅማቸውን ተጨባጭ ማድረግ የሚያስችል ቁርጠኝነት መፍጠር ቢችሉ ለሌሎች የሚተርፉበት ዕድልና አጋጣሚ ሰፊ ነው።

ከተደጋጋሚ የአየርንብረት ለውጥና ከዚህ ከሚመነጭ የድርቅ አደጋ እራሳቸውን ለመታደግ ያላቸው ዋነኛ አማራጭም ድርቅን የሚሸከም አካባቢያዊ /አገራዊ ኢኮኖሚ መገንባት ነው። ለዘለቄታውም ቢሆን ድርቅ በመጣ ቁጥር የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የልመና አጀንዳ ከመሆን የሚታደጋቸውም ይኸው ነው።

አሁን ያሉበትም ወቅቱ ይህንን እውነታ በተገቢው መንገድ ተገንዝበው፤ ለዜጎቻቸው ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ራሳቸውን በተሻለ መንገድ የሚያዘጋጁበት፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ይህንን አካባቢያዊ እውነታ መፍጠር እንዳይችሉ ተግዳሮት የሆኑባቸውን ፈተናዎች በአሸናፊነት ለመወጣት ከፍ ባለ ቁርጠኝነት ለመንቀሳቀስ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ነው።

በተለይም አካባቢውን ከግጭት ነፃ ቀጣና በማድረግ፤ የአካባቢው አገራት ሕዝቦች ለልማት ትኩረት በመስጠት ድርቅና ድርቅን ተከትሎ የሚከሰቱ አደጋዎችን ተቋቁመው መሻገር የሚችሉበትን ኢኮኖሚ እንዲገነቡ የሚያስችሉ አስቻይ ሁኔታዎችን በጋራ መፍጠር ይኖርባቸዋል።

ለዚህ የሚሆኑ የጋራ ፕሮጀክቶችን ከመቅረጽና ወጪን ከመጋራት ጀምሮ፤ የአገራቱን ሕዝቦች በተለያዩ መንገዶች በማስተሳሰር፤ በረጅሙ የግንኙነት ታሪካቸው ይዘዋቸው የመጡትን የጋራ ማኅበራዊ እሴቶች በማጠናከር ከፍ ሊል ለተገባው ቀጣይ ግንኙነታቸው አቅም አድርገው ሊጠቀሙበት ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አገር ማለት ለእኔ . . .

አስመረት ብስራት

ዛሬ፣ አገር ማለት . . . ለማለት የመፈለጌን ምስጢር ላመስጥር። እነሆኝ ጀምሬያለሁ . . . አገር ማለት በደምና በአጥንት የሚያቆሟት፤ ዋጋ ከፍለው፣ አኑረው የሚኖሩባት ስለመሆኗ ከዓድዋ ጀግኖች የተማርኩት በመኖሩ ነው «አገር ማለት» ለማለት የፈለኩት። ስንት ወገን ወድቆ፣ ስንት ደም ፈሶ፣ ስንት አጥንት ተከስክሶ፤ በክብር፣ በኩራት እንድንቆም ያደረጉንን ጀግኖች መዘከሪያ ወርሃ የካቲት እንደሆነ ስሰማ አገር ማለት ለማለት ወደድኩ።

አገር ማለት ለእኔ የተወለድኩበት ቦታ አይደለም። ድሄ፣ ዳዴ ብዬ ያደኩበት አፈር፤ አገር ማለት ለእኔ እትብቴ የተቀበረበትም አይደለም። ገና ከእናቴ ማህፀን ስወጣ ከለቅሶ ጋር የተነፈስኩት አየር፤ አገር ማለት ለእኔ ሌሎቹ እንደሚሉት ነፍስና ስጋ ነው - ሰው የሚሉት ቃል በፍቅር በአብሮነት በትብብር የሚኖርበት። አገር ማለት ለእኔ ከሳር ከቅጠሉ፣ ከጋራ ሸንተረሩ . . . ከሁሉም ይልቃል። ሰው የመሆን ምስጢር፤ ሰው የመሆን ዋጋ ዓድዋ ላይ ተከፈሎ ውድ የሆነው ደም እንደ ውሃ ፈስሶ ሌሎችን ቀና አድርጓል።

አገር ማለት ለእኔ ታሪክ ነው። ትዝታ፣ ከምዕተ አመት በፊት የተሳለ ሥዕል፤ የተወራ ትውፊት፤ የተቀመጠ እውነት በዓድዋ ተራራ ላይ በጀግኖቹ ደጃፍ ጨርቄን ማቄን ሳይል ልጅና ምሽቱን አስከትሎ የሄደው ሰው ያኛው ነው አገሬ፤ ዘርና ብሔር ሳይቆጥር፤ የማነህ፣ ከየት ነህ ያልተባባለበት፤ ሙስሊም፣ ክርስቲያኑ የሰው መሆን ትርጉም በደማቅ ቀይ ቀለም፤ ሊያውም በደም ሥዕል በዓድዋ ሽራ ላይ ላይደበዝዝ ደምቆ የተሳለበት ነው - አገር ማለት ለእኔ።

ከእናቴ ማህጸን የወጣሁበት ቀን፤ የሰማኋቸው ድምፆች፤ የእልልታው ድምቀት እሱ ነው አገሬ፤ ከእማማ ጊደይ ፈንድሻ፤ ከእትዬ መሪም የወሎ ጢስ፤ ከአዴ ጫልቱ ቤት መጥቶ እናቴ አናት ላይ የተቀመጠው ትኩስ የተናጠው ቅቤ፤ ከጎረቤቶቻችን ጋር ገንፎ ሲቋደሱ የነበረበት አንድ ትልቅ መአድ፤ ሁሉም ከበው በደስታና እልልታ አብሮ የሚቋደሰው . . . አገር ማለት ለእኔ አብሮ የሚኖር ሰው ነው።

አገር ማለት ለእኔ ትምህርት ቤት ሲሄድ የፊደል ገበታ ላይ ያየኋት ካርታ ናት፤ አገር ማለት ለእኔ ወደ ጎን ወደ ታች በቀጥታው መስመር የተፃፈው ፊደል ሳየው የሚያየኝ፤ ሳይገባኝ የማየው፤ በየኔታ ቅኝት ሀ...ሁ...ሂ.. ብዬ የቆጠርኩበት ዛሬ ላይ ቆሜ የእኔነቴ አሻራ በሌሎች መነፅር ምን እንደሚመሰል ከመጽሐፍ የማይበት፤ አገር ማለት ለእኔ ከየቤቱ መጥቶ በአንድ የተጋመደው፣ የእነ እገሌና የእነ እገሊት ልጅ ሳይባል በአንድ ቋንቋ የሚያወራው፣ የየኔታን ደጃፍ የረገጠው የልጆች እግር ነው።

አገር ማለት ለእኔ ከጓዴ ጀሚ ጋር አብረን የፆምነው የረመዳን ፆም ነው። የእኔ አገር ማለት የስቅለት ሰሞን ስግደቱን ላግዝሽ የተባባልንበት፤ እኔ ቁርሴን ካልበላሁ እሷ የምትተውበት፤ አገር ማለት ለእኔ በስጋ እንዳንለያይ ብዙ በዓላትን በስልስና እንቁላል አብረን የምናከብርበት፤ የጓደኝነት ገመድ ያስተሳሰረንን፣ እኔና ጀሚላን ያየዘን ፍቅር የሚገለፅበት፤ የጠዋቱን ስግደት ልትሰግድ ስትነሳ እኔንም ቀስቅሳ «በይማሪያም ሂጅና ቶሎ ተመለሽ፤ ቁርስ እንዳይረፈድብን» የተባባልንበት፤ የዩኒቨርሲቲ ግቢ . . . ለእኔ አገሬ እሱ ነው - ትንሿን ኢትዮጵያ የማይበት።

አገር ማለት ለእኔ ቋንቋ ነው፤ በአፍ የማይሉት በእዝነ ህሊና ብቻ የሚደመጥ አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ አፋርኛ፣ ቅማንትኛ፤ ጉራጊኛ ወይ ትግርኛ፣ የሚል ስም የሌለው በፍቅር ቋንቋ ብቻ አንድ የመሆን ዋጋ፤ የአንድ መቀመጫ፣ የአንድ መኖሪያ፣ የአንዱ መቀበሪያ፤ በመኖሯ ብቻ ፍቅርንም ፀቡንም የምናደርግባት ናት፤ የሁሉ እናት ጀርባ ሁሉን አዝላ ያለች አገር ማለት ለእኔ ያቺ ነች።

አማራውና አፋሩ፣ ኦሮሞውና ሲዳማው፣ ቋንቋዬን ባይሰማ፣ ባይገባው ባህሌም ግን ለቅሶዬን ሳይቀር፤ ሰርጌንም፣ ኀዘንና ደስታዬንም የሚጋራኝ ሰው ነው የኔ አገር። ሰው የተከፈለበት፣ የደም፣ የአጥንት ክብር፣ የቀይ ቢጫ አረንጓዴው የቃል ኪዳን ህብር ሕዝቦችን ከሰንደቃቸው አስተሳስሮ ያቆየ ያኛው ነው የእኔ አገር።

አገር ቅኔ ነው - ለእኔ የሁለንተናን አመስጥሮ ገበና ከቶ የሚይዝ፤ አገር ማለት ለእኔ የእናት ጓዳ ነው - ሲከፋኝ የምሸሸግበት፣ ሲደላኝ ተኳኩዬ፣ አምሮብኝ የምወጣበት፤ አገር ለእኔ ድግስ ነው - ሁሉ አብሮ በልቶ፣ ጠጥቶ የሚደሰትበት፤ አገር ለኔ ውርስ ነው - ከአያት አባት የተወራረሰ፣ ለእኔና ለአንተ ምቹ መኖሪያ፣ አባት ሲያቀና ቀዬና ቤቱን ሰርቶ ያስረከበበት።

ቤት መስሪያውም ምድር ጠላት ሲደፍራትም፣ ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፤ ብሔር፣ ዘር ሳይቆጥር ከሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች የተዋጣው፣ በእምዬ ምኒልክ ጥሪ ጥቅምት እኩሌታ ላይ ወረኢሉ የመሸገው፤ ብሎም ወደ ጦር ሰፈሩ፣ ወደ ዓድዋ የተመመው፣ ለዛሬው ክብር እንድንበቃ ደም አጥንቱን የገበረው፣ አገር ማለት ሰው (እሱ) ነው፤ ለእኔ የደምና የአጥንት ስሪት የሆነው።

> **አ**ገር ማለት ለእኔ ተፈጥሮ ከቸረው በረከት፣ የላቡን ፍሬ የሚበላ፤ አገር ማለት ወገን ነው - የእኔ የምለው መከታ። አገር ማለት ሰው ነው - አፈርን ገፍቶ ሲያበቃ በእጁ የያዘውን ፍሬ በእምነት ምድር ላይ የሚበትን ገበሬ፤ አገር ማለት ሰው ነው - በእምነት የተጣለው ፍሬ በቅሎ፣ ጎምርቶ ሲያሸት እሸት ቅመሱ ብሎ ሲያድል ያለስስት የሚኖረው ሰው፤

አገር ማለት ለእኔ ተፈጥሮ ከቸረው በረከት፣ የላቡን ፍሬ የሚበላ፤ አገር ማለት ወገን ነው - የእኔ የምለው መከታ። አገር ማለት ሰው ነው - አፈርን ገፍቶ ሲያበቃ በእጁ የያዘውን ፍሬ በእምነት ምድር ላይ የሚበትን ገበሬ፤ አገር ማለት ሰው ነው - በእምነት የተጣለው ፍሬ በቅሎ፣ ጎምርቶ ሲያሸት እሸት ቅመሱ ብሎ ሲያድል ያለስስት የሚኖረው ሰው፤ አገር ማለት ለእኔ ምርቱ የተሰበሰበ ዕለት በደቦ የሚያግዘው ጎረቤት ነው።

አገር ማለት ለእኔ ሰው በመሆንህ ብቻ አልቅሶ የሚቀብርህ፤ አገር ማለት ለእኔ ሦስት ቀናት ሙሉ የራሱን ቤት ትቶ ኀዘንህን እንድትረሳ ከጎን የሚቆምልህ፤ ጥቁር የሚለብስልህ፤ አገር ማለት ለእኔ የራበውን አጉራሽ የታረዘን አልባሽ ሰውና ሰው መሆን ብቻ የሚጠየቅበት፤ እሱ ነው አገሬ ቀባሪ ከፈጣሪ ተብሎ ሞት የማይፈራበት፤ አገር ማለት ለእኔ እጅ ለምፅዋት በተዘረጋበት ዕለት ያለምንም ስስት ኪስና ቦርሳውን የሚፈተሽባት፤ የእኔ አገር ይህ ነው። ከሰላምታ ጋራ ፈጣሪ ይመስገን ምላሽ የሆነበት፤ ለዛሬ መድረስን እንደ ታላቅ ስኬት የሚቆጠርበት፤ በምስጋና ብቻ ሕዝቡ በበረከት ኑሮን የሚኖርበት - ለእኔ አገር ያ ነው።

ልብ ስለአገር ብዙውን ያልማል፤ ቆም ብሎ ሲያስብ እውነቱ ግን ጠፍቷል፤ ሰው ባልተጠየቀበት ባልመረጠው ዘሩ ዛሬም ይጠላላል፤ ስለ አንድ አገር ቀርቶ በጎጥና ብሔር ይጎነታተላል፤ የዛሬ ቀንህ ላይ ለነገ የሚሆን ጉድጓድ ይቆፍራል፤ እንኳን አምኖ ሊቆም ለአንድነት ለክብሩ ጉርብትናም ጠልቷል። የታለች ያች አገር? በልቤ ውስጥ ነግሳ የታተመችው፤ የት አለች ያች አገር የደምና የአጥንት ዋጋ ያስከፈለችው? እኔን ግራ ገባኝ እናንተ መልሱ፣ አገሬ የት አለች ሰው የረከሰባት ዛሬ ላይ ሆናለች። አገር ሰው ከሆነ ሰው ለሆነው አገር ሰው ከተከፈለ የሰው ክብር ጠፍቶ ዝቅ ብሎ መታየት በዚህኛው ትውልድ ለምን ተፈጠረ? ብዬ አብቅቻለሁ።

# THANK YOU FOR WORKING WITH US!

**Dashen Bank** introduced the first interest free banking brand in Ethiopia by the name **Sharik**, means partnership, under the supervision of a shariah advisory committee, which was also the first of its kind in our Country. Dashen has achieved the following through its Sharik Interest Free Banking Service:

5th Sharik ANNIVERSARY

FIVE YEARS OF INCLUSIVE FINANCE

**60**
fullfledged interest free branches

**500,000+**
customers

ዳሸን ባንክ
Dashen Bank

**ETB 5 BILLION**
Interest free financing

**ETB 7 BILLION**
Deposits & investments

Sharik
የዳሸን ባንክ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት
Dashen Bank's Interest Free Banking Service

# የመማሪያ መጻሕፍት በወቅቱ አለመሰራጨቱ ለትምህርት ጥራት ተጨማሪ እንቅፋት ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር የአዲሱ ካሪኩለም የመማሪያ መጻሕፍት ስርጭት ሙሉ በሙሉ ሳይከናወን የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲቀጥል መደረጉ ለትምህርት ጥራቱ ተጨማሪ እንቅፋት ነው ሲሉ ዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ ገለጹ፡፡

በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የትምህርት አመራርና አስተዳደር መምህር ዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዲሱ ካሪኩለም መማሪያ መጻሕፍት በተለያዩ ክልሎች ላይ ተሟልቶ አለመቅረቡ በመማር ማስተማር ሒደቱ ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል።

እንደ አገር አዲስ ሥርዓተ ትምህርት የተቀረጸ ሲሆን፤ የመማሪያ መጻሕፍት ስርጭት ሙሉ በሙሉ ሳይከናወን የመማር ማስተማር ሂደቱ ሊገባደድ ወራቶች መቅረታቸው ሲታሰብ ለትምህርት ዘርፉ ፈተና መሆኑን መረዳት ያስችላል ሲሉ አብራርተዋል፡፡



ዶክተር አማኑኤል ኤሮሞ

አገሪቱ በትምህርት ጥራት ረገድ ያሽቆለቆለ ሁኔታ ውስጥ ገብታለች ያሉት ዶክተር አማኑኤል፤ በተጨማሪነት ደግሞ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መጻሕፍት ለተማሪዎች በበቂ ሁኔታ አለመድረሱ ችግሩን ያባብሰዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ያለመጻሕፍት የመማር ማስተማር ሂደትን ማስቀጠል ለመምህራንና ለተማሪዎችም ፈታኝ ነው፡፡ የስርጭቱ መጓደል ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ጋር በተገቢው መንገድ በትምህርት ይዘቶች እንዳይግባቡ ያደርጋል። በተለይ ከሌሎች ሰዎች እገዛን የሚፈልጉ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ላይ የችግሩ አሳሳቢነት ያይላል ብለዋል።

ባደጉት አገራት መጻሕፍት ባይታተሙም በቴክኖሎጂ ውጤቶች መጠቀም ይችላሉ፡፡ እንደ አገር በህትመት ችግር ምክንያት መጻሕፍት ባይኖሩ እንኳን በቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ዕድል መፈጠር ነበረበት ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የትምህርት ጥራት የሚረጋገጠው የተማሪ መማሪያ እና የመምህሩ መምሪያ መጻሕፍት ሲሟሉ ነው ያሉት ዶክተር አማኑኤል፤ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ከተማሪዎች እጅ ሳይደርስ ስለትምህርት ጥራት ማውራት በራሱ ስህተት መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር አማኑኤል ገለጻ፤ ትምህርት ሚኒስቴር የመማሪ መጻሕፍቱን በአነስተኛ ወጪ ለማሳተም ሂደት ላይ ቢሆንም የትምህርት ጥራት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ባለመሆኑ ህትመቱ እስከሚጠናቀቅ መጻሕፍቱን በጊዜያዊነት ሊተካ የሚችል መፍትሄ መዘጋጀት አለበት።

ህትመቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ መጻሕፍት በሶፍት ኮፒ እንዲደርሱ የተደረገ ቢሆንም መምህሩና ተማሪው ከቴክኖሎጂ ጋር መዋሀድ ባለመቻላቸው የተሻለ የትምህርት ግብዓት የሚገኝበትን አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ተጠቃሚ መሆን እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የመማሪያና ማስተማሪ መጻሕፍት መኖር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከመንግሥት ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መጻሕፍቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታትመው ለተማሪዎች እንዲደርሱ መሥራት አለበት ብለዋል፡፡

## የመንግሥት ልማት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ወቅትም እነዚህ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሀብታቸው ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ መመንደጉን አብራርተዋል።

‹‹የልማት ድርጅቶቹ አገር ናቸው›› ያሉት አቶ ሐብታሙ፤ ጠቅላላ እያንቀሳቀሱት ያለው ሀብት ከአንድ ትሪሊዮን ብር በላይ ሲሆን ከኖሚናል ጂ.ዲ.ፒ ውስጥ አስር ከመቶ የሚጠጋውንም የሚሸፍኑት እነዚህ ድርጅቶች መሆናቸውን አመልክተዋል። በየዓመቱም ለመንግሥት የሚያስገቡት ገቢ እጅግ ከፍተኛ ሲሆን፣ በአገሪቱ አጠቃላይ ዕድገት ላይ የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ።

በቻይና፣ ፈረንሳይ እና ሌሎች አገራትም የምጣኔ ሀብታቸው በትልቁ የሚዘወረው በመንግሥት የልማት ድርጅቶች መሆኑን ያስገነዘቡት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በኢትዮጵያም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ትልቅ አበርክቶ አላቸው፤ የሕዝብና የአገር ሀብትም ሆነዋል። ኢኮኖሚውን በመደገፍ ረገድም ሚናቸው የጎላ ነው። በቀጣይም በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጉልህ ድርሻ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል።

አገሪቱ የሪፎርም ሥራዎችን ከጀመረችበት ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ስብራት ለማስተካከል መንግሥት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን የገለፁት አቶ ሐብታሙ፤ ቀደም ሲል በኪሣራ ውስጥ የነበሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችም ትርፋማ መሆን ጀምረዋል።

የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ያለፉትን ስድስት ወራት የየተቋማቱን አፈፃፀም በገመገመበት ወቅትም በኪሣራ ውስጥ የነበሩ ድርጅቶቹ ወደ ትርፍ ህዳግ እየመጡ ሲሆን፣ በአመራርና በአሠራርም እየዘመኑ ይገኛሉ ብለዋል። ለአብነትም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሊዘጋ ተቃርቦ የነበረ ሲሆን ከሁለት ዓመት ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ ትርፋማ እየሆነ መጥቷል። የቀድሞው ሜቴክ (ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ) ኢትዮጵያን ከፍተኛ ቅርቃር ውስጥ አስገብቶ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ወደ ትርፋማነት ተሸጋግሯል። የአገሪቱን ገጽታ በማስተዋወቅ 127 ዓመታት ያስቆጠረው የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት እና ሌሎች ተቋማትም ከኪሳራ በመውጣት ትርፋማ ሆነዋል። የእነዚህ ተቋማት የኦፕሬሽንና የፋይናንስ አፈፃፀማቸውም አበረታች መሆኑንና ወጪ በመቆጠብ፣ ሀብት በማሰባሰብና ተጨማሪ ሀብት በመፍጠር ረገድም ውጤታማ መሆናቸውን አቶ ሐብታሙ አረጋግጠዋል።

ከተቋሙ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ፣ ብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት፣ ዕዳና ሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እና የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ናቸው።

## በተፈጠረው ሰላም የመስኖ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባላቸው በአንድ ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት በመስኖ ያለሟቸውን ሽንኩርት፣ በቆሎ፣ ሽንብራና ጎመን እያጠጡ ነው። በክልሉ የተፈጠረው ሰላም ለታታሪው አርሶ አደር በረከት ይዞላቸው እንደመጣ ይናገራሉ።

ከሁለት ዓመት በፊት ባላቸው ሁለት ሄክታር መሬት በመስኖ በማልማት ከፍተኛ ገቢ ያገኙ እንደነበርና ሞዴል አርሶ አደር ተብለው መሸለማቸውን የሚናገሩት አርሶ አደር ፀጋይ፤ ተከስቶ በነበረው የሰላም እጦት እንኳን የመስኖ ልማት ሊያካሂዱ ሕይወታቸውን ለማዳን ቤተሰባቸውን ይዘው አካባቢውን ለቀው ሄደው እንደነበር ገልጸውልናል።

አሁን በተፈጠረው ሰላም እንስሳቶቻቸውን ሸጠው ከነጋዴዎች አንድ ኩንታል ማዳበሪያ በ14 ሺህ ብር ገዝተው የመስኖ ልማት ሥራቸውን እንደገና መጀመራቸውን ነግረውናል። ጥረን ግረን ያመረትነውን ምርትም አብዛኛው የሚወስደው የማዳበሪያ ዋጋ ስለሆነ መንግሥት የማዳበሪያ አቅርቦት ድጋፍ ቢያደርግልን የተሻለ ለማልማት ብርታት ይሆነናል ብለዋል።

ሰላም ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለእንስሳቱም፤ ለዕፅዋቱም ያስፈልጋል የሚሉት አርሶ አደሩ፤ አሁን የተፈጠረውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ አርሶ አደሩም፤ ነጋዴውም፤ ተማሪውም፤ ጠብቆ ሊይዘው ይገባል። ሰላም ባይኖር ኖሮ አሁን ሁሉም ሥራውን እንደገና አይጀምርም፤ ለከፋ ችግርም ያጋልጣል፤ ስለዚህ ሁላችንም ሰላማችንን እንጠብቅ ሲሉ አርሶ አደር ፀጋይ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሽንብራና በቆሎ በመስኖ እያለሙ ያገኘናቸው ሌላኛው አርሶ አደር ስዩም ወልደፅዮን፤ የአርሶ አደር ፀጋይን ሀሳብ ይጋራሉ። ባላቸው አንድ ሄክታር መሬት በመስኖ የማልማት ሥራቸውን እንደጀመሩ የሚናገሩት አርሶ አደር ስዩም፤ ይህ የልማት ሥራ እየተሠራ የሚገኘው በትግራይ ክልል ሰላም በመፈጠሩ መሆኑን ነው የሚገልፁት። ዛሬ ላይ ከተረጂነት ለመላቀቅ የመስኖ ሥራችንን ዳግም ጀምረናል የሚሉት አርሶ አደሩ፤ የዕርዳታ እህል ከመጠበቅም የራስን አምርቶ እንደመመገብ የተሻለ አማራጭ ነገር የለም ነው ያሉት።

ናፍቆን የነበረው ሰላም አሁን ተፈጥሮልናል የሚሉት አርሶ አደር ስዩም፤ ከሁላችንም የሚጠበቀው ጠንክረን ሠርተን የተሻለ ምርት አግኝተን ገበያ ማቅረብ ነው ብለዋል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ማዳበሪያና ነዳጅ መሠረታዊ በመሆናቸው የመንግሥት ድጋፍ አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑንም ገልጸዋል።

መጪው ጊዜ የመኸር ወቅት በመሆኑ ከአሁኑ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ካልቀረበለት አስቸጋሪ ነው የሚሉት አርሶ አደሩ፤ መንግሥት ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ከአቀረበልን የእኛ ሥራ በትጋት የእርሻ ሥራችንን ማካሄድና ሰላማችንን መጠበቅ ነው ብለዋል።

በትግራይ ክልል ሰሜን ማዕከላዊ ዞን የታይታይ ቆራሮ ወረዳ የእርሻ ልማት ባለሙያ የሆኑት አቶ እዮብ ሙሉወርቅ፤ በተከሰተው ጦርነት የአካባቢው ሕዝብ ልማት ተስተጓጉሎና ለከፋ ችግር ተጋልጦ ቆይቷል። አሁን በተፈጠረው ሰላም ከአራት ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ቶሎ ወደ መስኖ ልማቱ ዳግም ተመልሰዋል። በወረዳው ከአንድ ሺህ 100 በላይ ሄክታር መሬት በመስኖ እየለማ ይገኛል።

አርሶ አደሩ ያጋጠመውን የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ችግር ተቋቁሞ ነው እያለማ የሚገኘው ያሉት አቶ እዮብ፤ የግብዓት ችግሮች ቢቀረፉ ከዚህም በላይ ማምረት እንደሚቻል ገልፀዋል።

## ባለ ማቀዝቀዣ ሕንፃው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ አቻ ደምሴ እንደገለጹት፤ ባለማቀዝቀዣ የቅይጥ ሕንፃ ግንባታው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚያግዝ ፕሮጀክት ነው።

የባለማቀዝቀዣ መጋዘን ግንባታው በ18 ወራት የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ከምድር በላይ አስር ወለሎችን የያዘ እና አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ደግሞ በአራት ዓመታት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ አስታውቀዋል።

ግንባታው ሲጠናቀቅ ኮርፖሬሽኑ ከአምራቹ የሚቀበለውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ያለብልሽት ጥራቱን ጠብቆ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል አቅምን ይፈጥራል ብለዋል።

አትክልትና ፍራፍሬ በቀላሉ የሚበላሽ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት ከምርት መነሻ ስፍራው አንስቶ እስከ ማከማቻ ቦታዎች ድረስ የማቀዝቀዣ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የግድ ይል እንደነበር አቶ አቻ አስታውሰዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትና መጠኑ ከፍ ያለ ምርት ሳይበላሽ በአንድ ስፍራ ለማከማቸት የሕንፃ ግንባታው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑን አስረድተዋል።

ሱቆች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ላብራቶሪዎችና ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ክፍሎች የግንባታው አካል መሆናቸውን የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ አምራቹ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን እንዲያመርት ለማበረታታት እና ያመረተው ምርት ሳይበላሽ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸጥ ለማድረግ ግንባታው አገራዊ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሐሰን መሀመድ በበኩላቸው፤ አገሪቱም ሆነ አምራቹ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ብልሽት ምክንያት የሚደርሰውን ኪሳራ ከመቀነስ በተጨማሪ ለማህበረሰብ ጤና ጠንቅ የሆኑ ችግሮችን በመከላከል ረገድ የባለ ማቀዝቀዣ ሕንፃ ግንባታው ሚና የጎላ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የማቀዝቀዣ መጋዘን ግንባታው አትክልትንና ፍራፍሬ ከብክነትና ከብልሽት ከመጠበቅ ጎን ለጎን ገበያውን በማረጋጋት የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስና ከውጭ የሚገቡት የታሸጉ ምርቶች በአገር ውስጥ ምርት በመተካት የወጪና ገቢ ንግድ እንዲመጣጠን ያደርጋል ሲሉ አስረድተዋል።

በተለይ ለገበያ ትስስርና ለዋጋ መረጋጋት ያለው ጠቀሜታ ጉልህ ነው ያሉት አቶ ሐሰን፤ የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ለኢኮኖሚው መረጋጋት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ቢሆንም ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ረገድ ብዙ መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

ባለ 10 ወለል ቅይጥ አገልግሎት ሕንፃ ግንባታውን ኤፍ ኢ ኮንስትራክሽን በተባለ አገር በቀል ድርጅት እንደሚገነባ ተገልጿል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ጽናትና ስኬት በዓለም አርት ጋለሪ

**ሰላማዊት ውቤ**

ልክ የላሊበላ ገዳማት መሠረት ከአናት እንደተጀመረው ሁሉ እኛም የዚህን ጽሑፍ ባለታሪክ ስናቀርብ ከስኬት ለመጀመር መረጥን።

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ከመገናኛ በኢምፔሪል ሆቴል አለፍ ብሎ ገርጂ ታክሲ ተራ በቅርብ ርቀት የሚገኘው "ዓለም አርትጋለሪ" ለአካባቢውና ከሩቅ ጭምር ለሚመጡ ወጣቶችና ጎልማሶች ፍሬያማ ተግባር በማበርከት ላይ ይገኛል። በዚህ ሥፍራ በአርት ጋለሪውም የሚከናወኑት ተግባራት በሀገር ደረጃ መስፋት ቢችሉ ምንኛ ጠቃሚ ይሆናሉ ብለን ራሳችንን ጠይቀናል። ለምን ብትሉ ወጣቶች፣ጎልማሶችና እድሜ ጠገብ የሆኑት እንኳ አስደሳችና ፍሬያማ ሰዓት የሚያሳልፉበት ሥፍራ በመሆኑ ነው።

ቤቱ በስዕሎች ፣ በመጽሐፍትና በመጽሔቶች የተሞላ ሲሆን ቡና ወይም ሻይ ለማለት የገባ እንግዳ በየጠረጴዛው ላይ ያሉ እርሳሶችንና ከለሮችን በመጠቀም የፈለገውን ስዕል ለመሳል ሙሉ ፍቃድ አለው። በተገልጋዮቹ ዘንድ ጋዜጣና መጽሔት የማንበብ ልምድም በብርቱ ዳብሮ ይስተዋላል። ብዙው ተገልጋይ እግረ መንገዱን ስለ ስዕል አሳሳል ጥበብ ከጋለሪው ባለቤት እንዲሁም የስዕል አስተማሪዎች ትውውቅና ምክርም ይደረግበታል። ተስተናጋጆች ስዕል እንዲሠሩ በእጅጉ ይበረታታሉ። በየግድግዳው ላይ የተንጠለጠሉት ስዕሎች ደግሞ ለእንግዶቹ የጨዋታ መጀመሪያና መወያያ ከመሆንም ባለፈ ትምህርት የሚሰጡ እንዲሁም ፍሬያማ የሆነ የዕውቀትና የውይይት መድረክ ሆኖላቸዋል። በጋለሪው ~~ውስጥ የስዕል~~ ሽያጭም ይከናወናል። ይህ ጋለሪ ተደናቂነትን ያተረፈ የስዕል ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ አቅርቧል ።

በጋለሪው በየሳምንቱ ቅዳሜ ከ11፡00 ሰዓት ጀምሮ የሚደረገው ውይይትና ክርክር ወጣቶች ሰብሰብ ብለው ስለ ስነጽሑፍ፣ቴክኖሎጂ ፣ ሳይንስ ፣ ማኅበራዊ ኑሮ፣ ሥነ ምግባር፣ ሙዚቃ፣ ፍልስፍናና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ልምድ እንዲሁም ሙያዊ ክህሎት ካላቸው ጋር ንግግሮችን የሚያደርጉ ሲሆን በሌሎች ጉዳዮች ላይም ገደብ የሌለው ውይይት ያደረጋሉ።

በየምሽቱ በሚደረገው ትምህርታዊ ንግግር (ሌክቸር)፣ ጥሩ መረጃ ይዞ መውጣት ያስችላል፤ በጥያቄና መልስ እንዲሁም ከተሰብሳቢው በሚሰጡ አስተያየቶች የዕውቀትና የትምህርት ገበያ ሆኖ ያመሻል ።

> **የ** አካል ጉዳተኞች አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ይችላሉ ብለው ከማስረዳት ጉዳታቸው ላይ ብቻ በማተኮር ትችላለህ ወይም ትችያለሽ ብለው ከማሳወቅና ከማስተማር ይልቅ ስለእግሮቻቸው ፣ ስለወገባቸው ፣ ስለእጆቻቸው፤ ሌሎች የአካል ጉዳቶቻቸውና ችግሮቻቸው ብቻ ደጋግሞ መናገር ይቀናቸዋል

የአርት ጋለሪው ባለቤት ሰዓሊ ዓለም ጌታቸው የምትሠራው በምክንያት ፣ በመረጃ፣ በዕውቀት የተገነባ ትውልድን መፍጠር ላይ ነው። "ይኼ ክፍተት በእጅጉ ጎልቶ በትውልዱ ይታያል ፤ስለሆነም ችግሮቹን በምክክር፣በውይይት፣ በንግግርና በክርክር የሚፈታና የሚማማር ትውልድን መፍጠር ወይም ማምጣት ያስፈልጋል » ስትልም ታክላለች።

ስስ ብልታችን በማኅበረሰብ ፣ በግለሰብ ፣ በሀገርም ደረጃ ቢሆን ይኼው ነው፤ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የድርሻችንን ለማበርከት በሚል በዚህ በኩል አበክረን እየሠራን እንገኛለን ስትልም ታስረዳለች ። በሀገር ደረጃ ከሚነሱት አንኳር ችግሮች መካከል የአቅም ማነስ፣ ሙሰኝነት ፣ ስርቆት ናቸው እነዚህ ደግሞ ከአስተሳሰብ ችግር የመጡ ናቸው ። ይህ የጋለሪው መርሐ ግብር ለጠራ አስተሳሰብ ነጥሮ መውጣት በብርቱ ይጠቅማል፤ አጀንዳዎች በዚህ አኳያ ይቀረፃሉ ስትል ታስረዳለች።

የሃሳብ ጥራት ያለው ትውልድ በዚህ ዓይነት ከመጣ የባሕል ለውጥ እየተፈጠረ፣ በዕቅድ የሚመራና በተግባር የሚንቀሳቀስ ትውልድ ተገኘ ማለት ነው። በምክንያት፣ በመረጃና ማስረጃ የሚነጋገር ባሕል ግንባታ ተካሂዷል ብሎም መውሰድ ይቻላል። በመሠረቱ ይህ ኢመደበኛ የሆነው የጋለሪ ባህል ዓይነተኛና መደበኛ የሆነውን የትምህርት ሥርዓት እንደሚያግዝም እንደምታምን ገልጻለች። ይህንን የአስተሳሰብ ችግር በመርሐ ግብራችን ካካተትናቸው አካል ጉዳተኞች ላይም ለመመልከት ችለናል፤ጥሩ ትምህርትም ተቀስሞበታል ስትልም ታነሳለች።

ከተለያዩ ቦታዎች ከጎዳናም ሆነ ከልመና ከየቤታቸው ከመጡትና ለትምህርትና ስልጠና ከያዟቸው አካል ጉዳተኞች አብዛኞቹ የአስተሳሰብ ችግር ያለባቸው ሰዎች ሆነዋል። ለአካል ጉዳተኞች የዊልቸር፣ የክራንችና ሌሎች.. ድጋፍ ብቻ ሊረዳቸውና ሊለውጣቸው አይችልም። በአካል ላይ የማይታየው የአስተሳሰብ ችግራቸው አንዱ መቀየር ያለበት ነው ፤ የማይታየው ጉዳት እሱ በመሆኑ። እሷ ዘንድ ካደራጀቻቸውና ማስተማር ከጀመረች በኋላ አዕምሯቸው ስለተጎዳ ወደ ነበሩበት ሥፍራ የመመለስ ችግር በተደጋጋሚ አይታለች ሰዓሊዋ። አዲሱን ሁኔታ ለመቀበል አዕምሯቸው በብርቱ ከብዶት እንደነበረም ያስተዋለችው ሐቅ ነው።በዚህ በኩል ያለውን ችግር ከምንጩ መፍታት ረዥም ስልጠና የሚጠይቅ እንደሆነም ታውቃለች። ይሁንና ከብዙ ጥረት በኋላ አሁን ላይ በትጋት አብረዋት የሚሠሩ ሰዎችን ማፍራት ችላለች። እሷን የጠቀሟት አዕምሯቸው የተለወጠ ሰዎች ናቸው ።

የአካል ጉዳተኞች አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ይችላሉ ብለው ከማስረዳት ጉዳታቸው ላይ ብቻ በማተኮር ትችላለህ ወይም ትችያለሽ ብለው ከማሳወቅና ከማስተማር ይልቅ ስለእግሮቻቸው ፣ ስለወገባቸው፣ ስለእጆቻቸው፤ ሌሎች የአካል ጉዳቶቻቸውና ችግሮቻቸው ብቻ ደጋግሞ መናገር ይቀናቸዋል። ነገር ግን ይሄ ለአካል ጉዳተኞቹም ሆነ ለራሳቸው ጠቃሚ አይደለም ። የችግሩን ሥረ-መሠረት እንዳላወቁት ማረጋገጫም ነው።

‹‹...... አባቴ መጽሐፍ አንባቢ ነበር፣እኔም እሱን አይቼ ማንበብ እወዳለሁ ፤ በልጅነቴ ከአጠገቡ ሁል ጊዜ ስለምገኝ ብዙ ነገሮችን በመለማመድ የመቻል ስሜት በውስጤ እንዲሰርጽ አድርጓል" ትላለች ሰዓሊዋ ዓለም ስለራሷና በአባቷ በኩል ውስጧ ስለወረሰው ተሞክሮዋን ስትገልጽ።

የአባት ውርስ ጥበቧ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አሁን ላለችበት የዕድገት ደረጃዋ ያደረሳት መሆኑንም አበክራ ስትናገር ትደምጣለች ፤ እሷ እንደምትናገረው ከሕፃንነት ዕድሜዋ ጀምሮ በተቀረፀባት ሕልምና እምነት አኳያ የተቃኘ አምስት ፕላትፎርም ያለው ጥርት ያለ የተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገኝ አድርጋዋለች። በአባቷ ውርስ የተቃኘው የራሷ ተሞክሮ ትልቁ የሕልሟና የአሁኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዋ መመሪያም ሆኗል።

### የመጽሐፍት ቤት

ሰዎች መጥተው መጽሐፍ ማንበባቸው በዚህም ትውውቅና ውይይት መከተሉ ብሎም የዕውቀት በር መከፈቱ አንዱ ነው። የተለያዩ አርዕስቶችን ተንተርሰው የተፃፉ መጽሐፍት በግዢ እንዲሁም በዕርዳታ በጋለሪዋ ውስጥ ተከማችተዋል። ወጣቶችም ሆኑ ጎልማሶች ወደ እሷ ጋለሪ በመምጣት በነዚህ መጽሐፍት የንባብ ፍላጎታቸውን ይወጣሉ፤ጋዜጦችና መጽሔቶችም ማግኘት ይችላሉ። ምርምር የሚሠሩ ወጣቶችም አብዝተው በቤተ መጽሐፍቱ ይጠቀማሉ ። ‹‹ዓለም አርት ጋለሪ›› ያለበት ሥፍራ በአካባቢው ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ የበዛበት በመሆኑ ለጋዜጣም ሆነ ለመጽሔት ንባብ የሚመጣው ቁጥር ከፍተኛ ነው።

### የስዕል ትምህርት ቤት

የስዕል ትምህርት ቤቱ ለሕፃናት ፣ ለወጣቶችና ለጎልማሶች የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ቀላል አይደለም ። ይሄ የስዕል ትምህርት ቤት ምስልን በዕውቀትና በመረዳት ሒደት ውስጥ አስፈላጊነትን ለማስረፅ የተደረገን የሰዓሊዋን ጥረት በብርቱ ያንፀባርቃል። ሰዓሊዋ እንዳጫወተችን ታዲያ የስዕል ትምህርት ቤቱ በርካታ ደረጃዎችን አልፏል። አሁን ራሱን ወደ ቻለ ትምህርት ቤትነት ለማደግም በቅቷል። ለአካባቢው ሕፃናት የነፃ የስዕል ትምህርት ይሰጣል፤ ወጣቶችና ሕፃናትን የክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ አስችሏል። ስዕሎቻቸውን ሲያጠናቅቁ ዐውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን) ስለሚያሳዩም ከፍተኛ መነቃቃት ፈጥሮባቸዋል። ሰዓሊዋም እንደምትለው ተማሪዎቻችንን ለክህሎቱ የሚኖራቸውን ፍቅር ከምናሳድግበት ዘዴ አንዱ ነው ስትል ትገልፀዋለች ።

### የአካል ጉዳተኞች ስልጠና

ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጠውን ስልጠና ጋለሪው ለብቻው ፈቃድ በማውጣት ጭምር የሚሠራበት ነው ። ሥልጠናው የሚካሄደውም በዚሁ በተናጠል ፈቃድ አውጥቶ በሚንቀሳቀስበት ቅኝት መሠረት ነው። አሁን በደረሰበት ደረጃ አርባ ለሚደርሱ በዊልቸር ፣ በክራንች የሚታገዙ አካል ጉዳተኞችን የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ በትጋት ይሠራል ። ‹‹ ከብዙ እልህ አስጨራሽ ሙከራ በኋላ ያገኘነው ትምህርት ቢኖር አካል ጉዳተኛ ማለት እጅ እግር የሌለው ፣ ወገቡ የማይንቀሳቀስ፣ በዊልቸር ታግዞ ወይም በክራንች ተደግፎ የሚሄድ ሳይሆን በአዕምሮው የተጎዳ ሰው መሆኑን ነው" ትላለች ስለ ውጤቱ ስትገልጽ። ይህ እሷ ያገኘችው ትምህርት በሌላ ቦታ እንደ ግብዓት ቢወሰድ ጠቃሚ እንደሆነም አበክራ ትገልጻለች።

### የሀሳብ መድረክ

ስለዚህ መድረክ ማብራሪያ ስትጀምር ‹‹መድረኩን ሌሎቹን ሥራዎቻችንንና እንቅስቃሴዎቻችንን ሁሉ እንደመስተዋት የምናይበት የዕድገታችን መለኪያ አድርገን እናየዋለን›› ትላለች። አክላም በየጊዜው በዚህ መድረክ የሚቀርቡ ሐሳቦች፣ ነጥቦች በምን ያህል ጥልቀትና ብስለት እያደጉ ነው ብለን ስንከታተል ድምር እንቅስቃሴያችን ራሱ የት ደረጃ ላይ እንዳለ ሁሉ እንገነዘባለን፤ ስለዚህም በበለጠ ለመሥራት፣ለመነሳሳት ስንቅም ሆኖናል። የሀሳብ መድረክ መርሐ ግብሩ በተለይ ሀገራችን አሁን ካለችበት ችግር አንጻር ወጣቱንም ሆነ ሌላውን ሰው በፍሬያማነት ሊያሳትፍ፣ ሊያነቃቃ የሚችል ነው። ጠቃሚነቱ ከፍተኛ ነው።

ስኬታማዋ የ "ዓለም አርት ጋለሪ" መሥራችና ባለቤት ዓለም ጌታቸው በዊልቸር የምትንቀሳቀስ ባለብሩህ አዕምሮ ኢትዮጵያዊት ሴት ስትሆን ዓለም በ 1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ወቅት ትንሽ ልጅ ነበረች። የተወለደችው በጎንደር ክፍለ ሀገር ሲሆን በልጅነት ዕድሜዋ ወደ አዲስ አበባ ከቤተሰቧ ጋር መጣች። ወላጅ አባቷ በደርግ ዘመን የሠራዊት አባልና በመካኒክነት የሚሠሩ ነበሩ። ዓለም ለቤተሰቦቿ ሁለተኛ ልጅ ስትሆን ሕመሟ የጀመራት በ12 ዓመት ዕድሜዋ ነው።

‹‹....... የጤናዬ ችግር ለረጅም ጊዜ ሳይታወቅ በመቅረቱ በቤት ውስጥ ለመቅረትና ለመዋል ተገድጄ ነበር። የኋላ የኋላ ግን በአከርካሪ (ስፓይናል ኮርድ) ላይ የደረሰ ችግር መሆኑ ታወቀ" ፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ አባቴ ከልጅነት ጀምሮ ማታ ማታ ከሥራ ሲመጣ ስዕል እንድሠራ ያበረታታኝ ነበር" ትላለች።

በሌላ በኩልም አባቷ መጽሐፍ ማንበብ ይወዱ ነበርና በልምድም ስዕል ይሞካከሩ ይህንን ሞክሪ ያንን ሥሪ እያሉ ሲገፋፏት ነው ያደገችው። ለዛሬ መሠረት የጣለላት መነሻዋ ይሄው መሆኑንም ታስታውሳለች። ለቤተሰቦቿ ሁለተኛ ልጅ ስትሆን ቤት ውስጥ ዘጠኝ ልጆች ነበሩ ። ታዲያ ከነሱ ውስጥ እሷ በሽታዋ ምክንያት በቤት ውስጥ ለረጅም ጊዜ ለመቅረትና ለመዋል መገደዷ ዛሬም ድረስ ከፊቷ ድቅን ይላል። ችግሯም በአከርካሪ አጥንትዋ ላይ መሆኑን ስታውቅ ደግሞ የተሰማትን



ሰዓሊ አለም ጌታቸው

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ተስፋ መቁረጥ የታያትን ጨለማ መቼም አትረሳውም ።

አሁን ላይ የተጎናፀፈችውን ብርሃናዊ ስኬትም ሊገዳደረው ሞክሮትም ነበር። ዓለም ሕመሟ አከርካሪዋ በመጎዳቱ ምክንያት መሆኑን የሰሙት የመንደሯ ሰዎች ደግሞ ገሚሶቹ ‹አትንቀሳቀሺ፣ አንዳንዶቹ መንቀሳቀስ ጥሩ ነው" በማለት ምክር ሲለግሷት መቆየታቸውን ታስታውሳለች። የዛሬዋ ዕውቅ ሰዓሊ በግራና ቀኝዋ በዚህ ሁኔታ ስትዋከብ ብዙ ዓመታት እንደዋዛ አልፈውባታል። ዓመታቱም ጉዳቷን የበለጠ አባብሰውታል። ቅስሟን ሲሰብሩት ፤ ስለልቦናዋንም በብርቱ ሲያደሙት ኖረዋል። ያም ቢሆን የአባቷ ተሞክሮ ትልቅ ጉልበት ሆኗት ያቋረጠችውን ትምህርት በተልዕኮ ለመከታተል በቃች።

‹‹...... አባቴ ከልጆቼ ሁሉ ባንቺ ነው የምተማመነው ይለኝ ነበር ፤ለአሁኑ ማንነቴ እርሾ የሆነኝ እሱ ነው፤ በልጅነቴ ትንሽ ወንበር ላይ ቁጭ ብዬ ስዕል ስሠራ የነበረው ይመስለኛል ›› በማለት ታወሳዋለች።

በዚህ ፍላጎትዋና ፍቅርዋ በመነሳሳት ለአራት ዓመታት በጣሊያኖች በሚተዳደር የስዕል (አርት) ገብታ ትምህርቷን በአዳሪነት ተምራ ዲፕሎማዋን አግኝታለች።ከምርቃት በኋላም በቅጥር ከነዚሁ አስተማሪዎቿ ጋር በመሆን በሻሸመኔ፣ ኩየራና በየገጠሩ እየተዘዋወረች ስዕልን ስታስተምር ቆይታለች። ጣሊያኖቹ ቆይታቸውን አጠናቀው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱም እርስዋ ወደ አዲስ አበባ ስትመለስ መልካም የሆነ አጋጣሚ እንደገጠማት ታስታውሳለች።

ዓለም ወደ አዲስ አበባ ከመጣች በኋላ ሥራ ለማግኘት ብትሞክርም ጨርሶ እማይቻልበት ሁኔታ አጋጠማት፤ አካል ጉዳተኛና በዊልቸር የሚንቀሳቀስን ሰው ለመቅጠር ፍላጎት ያለው ጠፋ፤ ‹‹...... ለሁለትና ሦስት ዓመታት በከባድ ችግር ውስጥ ነበርኩ›› ትላለች። ያ ወቅት ለእሷ ቤት ውስጥ ገብቶ ለመውጣት እጅግ አስቸጋሪ ነበር ። ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ዓይኑን አፍጦ ፤ጥርሱን አግጦ መጣ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ገርጂ መብራት ኃይል አካባቢ ሥራ የምትጀምርበት ሁኔታ ተፈጠረ።

‹‹..... በዚሁ ቦታ ራሴ የቀለም ቅብ ሥራዎችን እየሠራሁ ለግማሽ ወይም ለአንድ ሰዓት ያህል በበጎ ፈቃድ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን የስዕል አሳሳል ትምህርትን ማስተማር ጀመርኩ›› ስትልም አነሳሷን ታወሳዋለች። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወላጆች በጠየቁት መሠረት በተወሰነ ክፍያ ልጆችን ማስተማሩን ቀጠለች። እንዴውም የወላጆች ፍላጎትና ፈቃድ እየጨመረ በመምጣቱ የማስተማሪያ ቦታም እየጠበበ መጣ። በዚህ የተነሳ ሰፋ ያለ ሥፍራ መፈለግ ግድ አላት።

‹‹...... ከዚያም የነበርኩበትን ቦታ በመልቀቅ እዛው አካባቢ ወፍጮ ቤት በሚሰኝ ሥፍራ በተሻለ ሁኔታ ውስጥ መሥራቴን ቀጠልኩ፤ይህ ደግሞ ትምህርት ቤትም አርት ጋላሪም ሆኖ እንዲመቻች ጥረቴን ቀጠልኩ›› ትላለች። እንግዲህ በዚህ ጊዜ ነው ሰዓሊዋ አስተማሪዎችን ቀጥራ መሥራትም የጀመረችው። ቦታው የተሻለ በመሆኑ ለእሷም እንደ ልብ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላት። አሁን የአካል ጉዳተኞችንም በመርሐ ግብሯ በማካተት ማስተማር ጀመረች። ዓለም አሁንም ለእሷ ለራሷም ፤ ለማስተማር ለገቡትም መምህራን እንዲሁም አዲስ ለጀመሩት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በሰፊ ሁኔታ ለመማርና ለማስተማር የተሻለ ቦታ ደግሞ አስፈለጋት። ፤እንደውም በአካል ጉዳተኞች በኩል የተሻለ ሥራ ለመሥራት ራሱን የቻለ ፈቃድም አወጣች።

በዚሁ መሠረት ገርጂ ታክሲ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ እንድትመጣ የወረዳው አስተዳደር ፣ የቦሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ እገዛ አድርገውላታል፤ያለሸበት ቦታ አመቺ አይደለም በማለት በራሳቸው ተነሳሽነት ጭምር ለረዷት ምስጋናዋን ታቀርባለች።

በ 2004 ዓ.ም ነው ትምህርት ቤቱ የተመሠረተው፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመሠረታዊ የስዕል ትምህርት በየትኛውም የዕድሜ ደረጃ ያሉ 4ሺ ልጆችን አሰልጥናለች፤ አብረዋት የሚሠሩ ሰዎችም ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፤የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፤ አጫጭር ኮርሶችን ወስደው ኤግዚቢሽን እንዲያቀርቡ ታደርጋለች። በተለይ አንድ አበክራ የምትሠራበት ዘዴ ልጆቹ ሃሳብን የመግለፅ ችግር እንዳይኖርባቸው የምታደርገው የማስተማርና የማለማመድ ዘዴ ነው፤ "......ይኼ በጣሙን ጠቅሞናል፤ተማሪዎቻችን አዲስ ሃሳብ የማመንጨት፣ የመፍጠር አቅም እንዲኖራቸው አስችሏል" ትላለች።

ሴትነቴ አካል ጉዳተኛ መሆኔ ጥንካሬንና ኃላፊነትን ጨምሮልኛል ፤አባቴ ሠራዊቱ ከተበተነ በኋላ ታክሲ ሾፌር ሆኗል። ከልጅነቴ ጀምሮ እስከማስታውሰው ድረስ መልካም ንግግር ይናገራል፣ ለሕይወቴም መመሪያ የሆነኝ እሱ ነው፤ የአባቴ የአስተዳደግ ዘዴ እኔን ለውጦኛል ብዬ አምናለሁ፤አሁን ቤተሰቦቼን ሙሉ በሙሉ እማግዘቸው እኔ ነኝ፣ሰፊ ቤተሰብ ነው ያለኝ፤ጤንነቴን በተመለከተ እስከዛሬ እጅግም ጥረት አላደረኩም፤ በሀገራችን በነበረው ሁኔታ በጊዜው መታከም አልቻልኩም፤ፊዚዮቴራፒ ጀምሬ ነበር ግን ትንሽ ችግር ፈጠረብኝ፣ በዚህም የተነሳ አልቀጠልኩበትም።

በድርጅቱ ካፌ ውስጥ ሥራ የተፈጠረላቸው በርካታ ሠራተኞች አሉ፣ አስተማሪዎች እየገቡ እየወጡ ስለሚሠሩ በአሁኑ ሰዓት ከ15 የማያንሱ መምህራን አሉ፤በሃሳብ መድረኩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉም እንዲሁ በጋለሪው ይገኛሉ። ወጣቶች በዚህ በኩል የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ መርሐ ግብር ከማሳወቁ ጀምሮ አጀንዳዎቹን ለተጠቃሚዎች በማስተላለፍ ይሠራሉ፤ እንዲሁም በጣም በተሳለጠ መንገድ መድረኩ በማዘጋጀትና በማቀናበር ይተጋሉ፤መርሐ ግብሩን በዝግጅት የሚያግዙ ሌሎች ሰዎችም አሉ፤ በጥቅሉ በጋላሪው ከ 25 በላይ ሠራተኞች አሉ ፤ በሥነ ጥበቡም ቢሆን እንዲሁ የሚተጉ ብዙ ልጆች አሉ፤ወጣቶች ለምክር፣ ለመማር በመደበኛ ወይም በኢመደበኛ መንገድ ወደ እሷ ይመጣሉ። በአምስት ፕላትፎርም ላይ እየሠራ ያለው ድርጅቷ በመንግሥት ደረጃ ሊሠራበት የሚገባ ነው። ሰዓሊዋ ቦታ ከመንግሥት ለመጠየቅ እየሞከረች ነው።

## ምስክርነት

ወጣት ራሄል ሸባባው ከዓለም ጋር ለረጅም ጊዜ የሰራችና አሁንም በጋራ እየሰራች ያለች ወጣት ነች። ራሄል በሙያዋ ሁለገብ አርቲስት ነች። የፊልም ስክሪፕቶችን ታዘጋጃለች። ስዕልም ትስላለች። ስዕል መሳል የጀመረችው ግን ወደ ዓለም ጋለሪ ከመጣች በኋላ ነበር። ጊዜውን ስታስታውስም እንዲህ ነበር ያለችን ‹‹ስዕል የለመድኩት በእንግድነት የስዕል ሥራዎቿን ላይ በመጣሁበት አጋጣሚ እርሳስና ወረቀት ተሰጥቶኝ ነው። ስዕል አልችልም ብልም እሷ ነበረችና ሞክሪ አለችኝ። ሞከርኩ። በወቅቱ የሰራሁትን ባላስታውስም አበረታታችኝ። ከዚህ በኋላ ደጋግሜ ወደ እሷ እየሄድኩ ሥዕል አሳሳል ጥበብን መማር ጀመርኩ። አሁን በእርግጠኝነት ስዕል መሳል ችያለሁ››

ወጣቷ ራሄል አሁን ዓለም ጋለሪ ውስጥ በቋሚነት ትሰራለች። ከዓለም ጋር በሀሳብ መድረክም ሆነ በስዕል አብራ ትጓዛለች። የተለያዩ ሀሳቦችን በማመንጨትም ታግዛታለች።

ዓለም ጋር በርካታ በጎ ፈቃደኞች እየመጡ አብረዋት ይሰራሉ። በሙያው ሐኪም የሆነው ክርስቲያን እንዳለ ከበጎ ፈቃደኞቹ ውስጥ አንዱ ነው። ክርስቲያን እንደነገረን፤ ዓለም ሴትነትና አካል ጉዳተኝነት ሳይገድባት ህልሟን ወደ ተግባር ለውጣ ለስኬት የበቃች ጠንካራ ሴት ናት። ሕብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኞች ያለውን የተሳሳተ አመለካከትና ንቀትም ሰብራ መውጣት ችላለች። የምትሰራቸው ስዕሎች በራሳቸው ድንቆች ናቸው። ልዩ ውበትም አላቸው።

ዓለምን የተለየች ሴትና ሰዓሊ የሚያደርጋት ይሄን ችሎታዋን ሁሉም ሰው እንዲጋራት መፈለጓ ነው። ፈልጋ ሳትቀርም በእንግድነትም ሆነ በሌላ ለመጣ ወረቀትና እርሳስ በማቅረብ እንዲሰሩ ብርታት የምትሰጥ እንስት ናት። እርሱ እርሷ ጋር የመጣው በድንገት ነበር። ሆኖም በጎነቷና ጥረቷ ስቦት ከእርሷ ላለመነጠል ወሰነ። በዚህም አሁን ላይ ጥረቷን ከማድነቅ አልፎ በሙያው በበጎ ፈቃደኝነት እያገዛት ይገኛል።

> **ልጆቹ ሃሳብን የመግለፅ ችግር እንዳይኖርባቸው የምታደርገው የማስተማርና የማለማመድ ዘዴ ነው፤ —......ይኼ በጣሙን ጠቅሞናል፤ተማሪዎቻችን አዲስ ሃሳብ የማመንጨት፣ የመፍጠር አቅም እንዲኖራቸው አስችሏል“ ትላለች**

ወጣት ታረቀኝ መኮንንም የዓለም ውለታ ካለበት ሰዎች መካከል ነው። ምክንያቱም በዓለም ጋላሪ የሥራ ዕድል ተፈጥሮለታል። እርሷ ጋር ከተማሩት ልጆች መካከል በመሆኑም አሁን ላይ በጋለሪው ውስጥ የስዕል ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛል። የወር ደሞዝተኛም ነው። ስለ ዓለም ብርታትና ጥንካሬ ተናግሮ አያበቃም። ዓለም የብዙ ሰዎች እናት እንደሆነች ያምናል። ምክንያቱም የስዕል ባለሙያ ወጣቶችን አፍርታለች ፤ ከዚያም አልፎ የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ጭምር እንዲሰሩ ሆነዋል። ለዚህም አብነቱ ራሱ ነው።

ኪሩቤል በቀልና ሰላማዊት ፍቅሩ በዓለም ጋለሪ ያጠመደ አያጣቸውም። የ18 ዓመቷ ወጣት ሰላማዊትም ሆነች ዕድሜው 36ኛውን የያዘው ኪሩቤል አካል ጉዳተኞች ናቸው። ሁለቱም በዊልቸር ነው የሚሄዱት። ሁለቱም የስዕል ተማሪዎች ናቸው። በጋለሪው መገኘታቸውም አይደንቅም። ነገር ግን ከትምህርት ሰዓትና ቀናትም ውጭ ከዓለም ስር ስር እያሉ ዕውቀት ሲቀስሙ ነው የሚውሉት። በፍፁም ከእሷ መለየት አይፈልጉም።

ሰላማዊት ምክንያቷን ስትገልጽ ‹‹እኔ የአካል ጉዳተኛ በመሆኔ እንኳን ስዕል በመሳል ታዋቂ ልሆን ከሰው ጋር በአንድ ላይ መዋል እችላለሁ የሚል ዕምነት አልነበረኝም። ዓለም ራሴን ደብቄ ካለሁበት ድረስ መጥታ ነው ይሄን አስተሳሰቤን ልትቀይርልኝ የቻለችው። በመሆኑም እንዴት ይህችን ሴት መራቅ ይቻላል? ስትል ትጠይቃለች። ሁልጊዜ ከስሯ የማትለየውም ለዚህ እንደሆነ ትናገራለች። ዘንድሮ ሦስተኛ ዓመቷን ጨርሳ በሙያው ለመመረቅ የቻለችውም በዓለም መሆኑን ትመሰክራለች። ከአምስት ጊዜ በላይ የስዕል ኤግዚብሽን ለማሳየት የረዳቻት ዓለም መሆኗንም አጫውታናለች።

ኪሩቤል እንዳለንም እንደ ሰላማዊት ከአራት ጊዜ በላይ ኤግዚብሽን ማሳየት የቻልኩት በዓለም ነው። አሁን ጥሩ ሰዓሊ ሆኛለሁ። የአካል ጉዳት ከምንም ነገር እንደማይገድብም በዓለም ተምሪያለሁ ይላል፡፡ ወደ ዓለም ተመልሰን ጽሑፋችንን ስናሳርግ ማዕከሉን ለመሥራት እጥራለሁ፣ ለትውልድ መልካም ነገር ለማስቀረት እፈልጋለሁ" ትላለች ።

# ባህልና ቱሪዝም

# ዓድዋ - ያልተጠቀምንበት ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ

**ሶሎሞን በየነ**

አውሮፓውያን በፈረንጆቹ 1884 እና 1885 በጀርመን በርሊንግ ከተማ አፍሪካን እንደ ቅርጫ ስጋ ከፋፍለው በቅኝ ግዛት ለመቀራመት የአህጉሪቷን ካርታ ዘርግተው ዕጣ ተጣጣሉ። ሕልማቸው ሰምሮም ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የአፍሪካ ሀገራትን በቅኝ ግዛት ሥር አዋሉ። ኢትዮጵያን ለመውረር ቀይ ባሕርን አቋርጦ የመጣው የጣሊያን ወራሪ ጦር ግን ያልጠበቀው ዱብዳ ገጠመው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአራቱም ማዕዘን ቀፎው እንደተነካ ንብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ በ1888 ዓ.ም የካቲት 23 ቀን (ከ1895 እስከ 1896 እ.ኤ.አ.) ዓድዋ ላይ የጣሊያንን ጦር ገጥሞ ድል ያደረገበት 127ኛው የዓድዋ ድል በዓል እነሆ ዘንድሮ “አንድነት፣ ጀግንነት እና ጽናት!” በሚል መሪ ቃል በሀገር አቀፍ ደረጃ በደማቅ ሥነሥርዓት ተከብሯል፤ ከኢትዮጵያም አልፎ በአውሮፓና በአሜሪካ አደባባይ በዓሉ ተከብሯል።

ይህን የመላው የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ቀንዲልና የትግል ዓርማ የሆነውን የዓድዋ ድል በዓል በየዓመቱ ታሪኩን በመዘከር በኩል ብዙ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ድሉ ግን ከዚህም ባለፈ መልኩ መዘከር ይኖርበታል፡፡ ብዙ ሊዘከሩት የሚገባቸው ተግባሮች መከናወን ይኖርባቸዋል ሲባልም ቆይቷል፤ ይህን ተከትሎም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግዙፍ ሙዚየም እየገነባ ነው፡፡ በትግራይ ክልል በዓድዋ ከተማም የፓን አፍሪካን ዩኒቨርሰቲ ለመገንባት የተጀማመሩ ሥራዎች እንደነበሩም ይታወቃል፡፡

ድሉን ለተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ ዓላማዎች ማዋል እንደሚቻልም እየተገለጸ ነው፡፡ በተለይ ለቱሪዝም ዘርፉ በማዋል ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚቻል በተለያዩ ወገኖች ይጠቆማል፡፡

የቱሪዝም ከፍተኛ ባለሙያና ተመራማሪው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) እንደሚሉት ፤ የዓድዋ ድል ታሪካዊ ዳራን ስንመለከት በዓሉ የመላው የጥቁር ሕዝብ የድል በዓል ነው። ኢትዮጵያውያን የጣሊያንን ጦር ዓድዋ ላይ ገጥመው ድል ያደረጉት የአፍሪካ ሀገሮች በሙሉ በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ውስጥ እያሉ ነበር። ይህ ድል ለሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች “ለካ ጥቁሮች በነጮች ላይ ድል መቀዳጀት ይችላሉ” የሚለውን ግንዛቤ ወስደው ለነጻነታቸው ለመታገልና ነጻነታቸውን ለማወጅ ከፍተኛ መነቃቃት ፈጥሮላቸዋል፤ በርም ከፍቶላቸዋል። በዚህም የአፍሪካ ሀገሮች ኢትዮጵያን የነፃነታቸው ዓርማ አድርገው ስለሚቆጥሯት ከ29 በላይ ሀገራት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በተለያየ መልኩ ብሔራዊ ዓርማቸው አድርገው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

> ይህን የመላ የጥቁር ሕዝብ የድል በዓል በየዓመቱ ታሪኩን ዘክሮ ከማለፍ ባለፈ እሴት ተጨምሮበት ለሀገርና ለሕዝብ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ማድረግ የሚቻልባቸው ፈርጀ ብዙ መንገዶች አሉ ። ከነዚህ መካከል የዓድዋ ድል በዓልን እንዲሁም ድሉ የተገኘበት ቦታን ለቱሪስት መስሕብነት በማዋል ከዘርፉ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት፣ በዚህም ማኅበረሰቡንም መጠቀም ይቻላል

በመሆኑም ይህን የመላ የጥቁር ሕዝብ የድል በዓል በየዓመቱ ታሪኩን ዘክሮ ከማለፍ ባለፈ እሴት ተጨምሮበት ለሀገርና ለሕዝብ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ማድረግ የሚቻልባቸው ፈርጀ ብዙ መንገዶች አሉ ። ከነዚህ መካከል የዓድዋ ድል በዓልን እንዲሁም ድሉ የተገኘበት ቦታን ለቱሪስት መስሕብነት በማዋል ከዘርፉ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት፣ በዚህም ማኅበረሰቡንም መጠቀም ይቻላል።

ለዚህም ጦርነቱ የተካሄደበት ወይም ድሉ የተገኘበት ቦታ ዓድዋ ነው። በዚህ ቦታ ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በዓሉን ከመዘከር ባለፈ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ጎብኚዎች ዓመቱን ሙሉ በቦታው ተገኝተው እንዲጎበኙ ቦታውን ማልማት ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ሲሳይ፣ ቦታውን የቱሪስት መስሕብ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ማግኘት ይቻላል ይላሉ።

እንደ ዶክተር አያሌው ገለጻ፤ ሌላው የጦርነቱ የታሪክ አካል የሆኑ መልክዓ ምድሮችን፣ ከፍተኛ የጦር አመራሮች የተሰዉባቸውን ቦታዎች፣ ወ.ዘ.ተ ታሪኩን መሠረት አድርጎ በማልማት የቱሪስት መስሕብ ማድረግ ይቻላል። ለአብነት የውጫሌ ስምምነት የት ተካሄደ? ስምምነቱ እንዴት ፈረሰ? ጄኔራል አልቤርቶኒ የተማረከበት እና ጄኔራል ዳቦርሜዳ የተገደለበት ቦታ የት ነበር? እንዲሁም ሶሎዳ፣ አባ ገሪማ፣ ኪዳነምሕረት፣ ራዕይዩ የሚባሉ ጦርነት የተካሄደባቸው ተራራዎች ላይ ምን ምን ታሪክ በቦታው እንደተሠራ? በሚገልጽ መልኩ በማልማት የቱሪስት ሳይት ማዘጋጀት ይቻላል። በተለይ እነዚህ ቦታዎች የእግር ጉዞ አድርገው ለሚጎበኙ ጎብኝዎች ተመራጭና ሳቢ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ያኔ ምንም ዓይነት የመገናኛ ወይም የመረጃ መለዋወጫ ቴክኖሎጂ በሌለበት በአጭር ጊዜ ውስጥ “እንዴት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የክተት አዋጁን ተቀብለው ወረኢሉ ከተው ጠላትን ሊመክቱ ቻሉ” የሚለው በራሱ አንድ የቱሪስት መስሕብ የሚሆን ታሪክ ነው። ስለዚህ መጀመሪያ አምባላጌ ላይ የተደረገው ጦርነት ምን ይመስል ነበር? ከአምባ ላጌ ቀጥሎ ጦርነቱ ወደ መቀሌ እንዴት አመራ? ከመቀሌስ እንዴት ወደ ዓድዋ ጦርነቱ አምርቶ መቋጫ አገኘ? የኢትዮጵያ ጦር የዓድዋ ተራራን በምን መልኩ እንደተገን ተጠቅሞ ድል ሊያደርግ ቻለ? የሚሉትን በሙሉ የጦርነቱን ታሪክ የሚተርክ የቱሪስት መምሪያ መጽሐፍ (Tourist guide book) ቢዘጋጅ ታሪኩ የሀገር ውስጥንም የውጭውንም ጎብኚ የሚመስጥ ይሆናል። በዚህም ራሳቸውን ጣሊያኖችንም መሳብ ይቻላል። የሌላውንም ዓለም ቀልብ ይገዛል።

በዚህም “በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ” እንዲሉ ድሉ የተገኘበት ቦታ፣ የጦርነቱ አካል የሆኑ ታሪካዊ ቦታዎችን እና መልክዓ ምድሮችን ጎብኚዎች ለመጎብኘት ወደ ቦታው ሲያቀኑ እግረ መንገዳቸውን በአካባቢው ያሉ ሌሎች የቱሪስት መስሕብ ቦታዎችን ይጎበኛሉ። ይህም ለአካባቢው ማኅበረሰብ ኢኮኖሚ መነቃቃት ትልቅ ፋይዳ የሚኖረው ከመሆኑ በዘለለ ለወጣቶች ሰፊ የሥራ እድል ይፈጠርላቸዋል።

ከዚህ አኳያ ቀደም ሲል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሑራን ጦርነቱ ከተካሄደባቸው የዓድዋ ተራራዎች አንዱ የሀገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ ቦታ እንዲሆን ለማስቻል ጥናት አካሂደው ነበር። ታሪካዊ ዳራውን መሠረት ያደረገ ደረጃውን የጠበቀ የቱሪስት መምሪያ ተዘጋጅቶ ለአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ለአስጎብኚዎች እንዲሁም ለቄሶች ጭምር ስልጠና ተሰጥቶ ነበር። በዚህም የአካባቢው ማኅበረሰብ “ቦታው የቱሪስት መዳረሻ ሊሆንልን ነው” ብሎ ደስ ብሎት በጣም ተስፋ አድርጎ ነበር።

ጥናቱ ግን ወደ ተግባር ሳይቀየር ቀርቷል ያሉት ዶክተር አያሌው፣ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደውን ጥናት መሠረት በማድረግ ቦታውን አልምቶ ወደ ቱሪስት መዳረሻነት በመቀየር ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወደሚያስገኝ መንገድ መቀየር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ከኅዳር አጋማሽ እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት ያለበት ወቅት መሆኑን የሚናገሩት የቱሪዝም ባለሙያው፤ እነዚህ ወራት በተለይ በምዕራቡ የዓለም ክፍል በጣም ቀዝቃዛና በረዷማ ወቅት ናቸው። በዚህ ወቅት ምዕራባውያን ከዚህ የአየር ንብረት ለመራቅ ሞቃታማ የአየር ንብረት ወዳላቸው ሀገሮች ለጉብኝት ይጎርፋሉ። በዚህ ወቅት ለጎብኚዎች ተመራጭ ከሆኑ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ በግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናት ሲሉ ያብራራሉ።

ምክንያቱ ደግሞ በነዚህ ወራት የአየር ንብረቷ ተስማሚ ከመሆኑ ባለፈ እንደ ገና እና ጥምቀት ያሉ ኃይማኖታዊና የአደባባይ በዓላት የሚከበርበት ወቅት በመሆኑ ነው ያሉት ዶክተር አያሌው፣ ስለዚህ በዚህ ወቅት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የውጭ ጎብኚ ወደ ሀገሪቱ ይገባል። በአንጻሩ በዩ.ኔ.ስ.ኮ በማይዳሰስ የዓለም ቅርስነት የተመዘገበው የመስቀል በዓል የሚከበረው መስከረም ወር ላይ ነው። ይህ ወር በምዕራባውያን ዘንድ ሞቃታማና ተስማሚ የአየር ንብረት ያለበት ወቅት ስለሆነ እምብዛም የውጭ ጎብኚዎች በበዓሉ አይታደሙም። ስለዚህ ከኅዳር አጋማሽ ጀምሮ ታኅሣሥ፣ ጥርና የካቲት ወራት በሀገሪቱ ከፍተኛ የጎብኚዎች ፍሰት ያለበት ወቅት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በመሆኑም የዓድዋ ድል በዓል የሚከበረው ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት ያለበት ወቅት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ ስለዚህ እንደ መስቀል፣ ጥምቀት፣ ኢሬቻ፣ ጨምበላላ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ የአደባባይ በዓላት ሁሉ የዓድዋ ድል በዓልን በተመሳሳይ መልኩ በማክበር የቱሪስት መስሕብ ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ማመቻቸት እንዳለባቸው ሲሉ ያመለክታሉ። ምክንያቱም የውጭ ጎብኚዎች ለገናና ለጥምቀት በዓላት ወደ ሀገሪቱ በከፍተኛ መጠን የሚገቡበት ወቅት ስለሆነ ቱሪስቶቹ በቀላሉ የቆይታ ጊዜያቸውን አራዝመው የዓድዋ ድል በዓልን እንዲታደሙና የዓድዋ የቱሪስት መስሕብ ስፍራዎችን እንዲጎበኙ ማድረግ ይቻላል ይላሉ።

የዓድዋ ድል በዓልን የቱሪስት መስሕብ ለማድረግ ከዚህ ቀደም እዚህ ግባ የሚባል ሥራ እንዳልተሠራም ጠቅሰው፣ ስለዚህ ድሉን በየዓመቱ ከመዘከር ባለፈ የቱሪስት መስሕብ ለማድረግ የበዓሉ አከባበርና የማስተዋወቅ ሥራው ምን መምሰል እንዳለበት? ለወደፊቱ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ሌላው ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ አንጻር “እንዴት የዓድዋ ድል በዓልን ለቱሪስት መስሕብነት ማዋል ይቻላል” በሚለው ላይ የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው እንዳብራሩት፤ ምዕራባውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት ተቆጣጥረው የባሪያ ንግድ ሲያጧጡፉ በነበረበት ወቅ ጋናን የባሪያ ንግድ አስኳል አድርገው ገበያውን ያጧጡፉት ነበር። ጋና ይህን ጥቁር ጠባሳዋን “Root of Slave Tread” በሚል ለቱሪስት መስሕብነት እያዋለችው ትገኛለች። ይህም ጋናዎች “አሁን ያሉት የምዕራባውያን ዜጎች አባቶቻቸው የባሪያ ንግድ ይፈጽሙበት የነበረውን ቦታ በመጎብኘት ለተበዳዩ የጥቁር ሕዝብ በቱሪዝሙ መካስ አለበት” ብለው የፈጠሩት የቱሪዝም መስሕብ ነው። በዚህም ጋና ይህ ሥፍራዋ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ የምታገኝበት አንዱ ምንጪ ነው።

ስለዚህ ጋና ጥቁር ጠባሳዋን ወደ ገቢ ምንጭነት መቀየር ችላለች። ነገር ግን ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ቀንዲልና የትግል ዓርማ የሆነውን የዓድዋ ድል በዓልን ከመዘከር ባለፈ ፋይዳ ያለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ አልቀየረችውም። ስለዚህ ከጋና እንዲሁም ከሌሎች ሀገሮች ልምድ በመቅሰም ይህን ታላቅ የመላ ጥቁር ሕዝብ የድል በዓል ለቱሪዝም መስሕብነት ማዋል የሚቻልበት ዘርፈብዙ እድሎች አሉ ሲሉ ይጠቁማሉ።

የመጀመሪያው ልክ እንደጋና አሁን ያለውን የጣሊያን ትውልድ በወንድማማችነት መንፈስ ኢትዮጵያን እንዲጎበኝ በመጋበዝ ትናንት አያት ቅድመ አያቶቻቸው የወደቁበትን ቦታ እንዲጎበኙ እና በዓሉን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲያከብሩ በማድረግ የቱሪስት ፍሰቱን ከማሳደግ ባለፈ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ እንዲጠናከር ማድረግ እንደሚቻል ዶክተር አያሌው አመልክተዋል። በዓሉን ከሀገሪቱ ታሪካዊ እና ባሕላዊ ዐውድ ጋር በተስማማ መልኩ በየዓመቱ በማዘጋጀት በቱሪስት ተመራጭ የሆነ መስሕብ ማድረግ እንደሚቻልም ይጠቁማሉ። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተገነባ እንዳለው የዓድዋ ሙዚየም ያሉ ፕሮጀክቶች ነገ ላይ በከፍተኛ መጠን የሀገሪቱን የቱሪስት ፍሰት የሚጨምሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ስለዚህ መሰል ፕሮጀክቶችን ማስፋት ያስፈልጋል ይላሉ።

በአጠቃላይ በዓሉ ከኢትዮጵያ አልፎ በአውሮፓና በአሜሪካ አደባባይ በድምቀት መከበሩ በዓሉን በስፋት ለዓለም ሕዝብ በማስተዋወቅ የቱሪስት መስሕብ ለማድረግ ትልቅ እድል ይፈጥራል። በመሆኑም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በዓሉን ሲያከብሩ የጀግኖች አባቶቻቸውን የጦር ሜዳ አልባሳት ለብሰው ባሕላቸውን ከማሳየት ባለፈ በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ስትራቴጂ ነድፈው ድሉን ለዓለም ማኅበረሰብ በማስተዋወቅ ለበዓሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጎብኚ ወደ እናት ሀገራቸው እንዲመጣ ማድረግ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ።

በውጭ የሚኖሩ ዜጎችን በማስተባበር ያለምንም ወጪ እነርሱን ተጠቅሞ በዓሉን በከፍተኛ ሁኔታ የማስተዋወቅ ዘመቻ ማከናወን እንደሚቻል አመልክተው፣ ስለዚህ “በእጅ የያዙት ወርቅ …” እንዲሉ “ዓድዋ በእጃችን ያለ ነገር ግን ያልተጠቀምንበት ጭስ አልባው የኢንዱስትሪ ወርቅ ነው። ይህን በእጃችን ያለ ወርቅ እሴት ጨምሮ በማልማት ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንደሀገር ማግኘት” እንደሚቻል የቱሪዝም ባለሙያው ይናገራሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# የዓድዋ እና ካራማራ ድሎች

**ዋለልኝ አየለ**



ዓድዋ



ካራማራ

እነሆ የየካቲት ወር ገናናው ታሪኩ ላይ ደርሰናል። በዚህ ሳምንት ባሳለፍነው ሐሙስ የካቲት 23 ቀን የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለም የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ የሆነውን የኢትዮጵያን የድል ቀን ዓድዋን በድምቀት አክብረናል። ዓድዋ ብዙ የተባለለትና ብዙ ሰው የሚያውቀው ቢሆንም «ዓድዋ ዛሬ ናት ዓድዋ ትናንት» ስለተባለለት ታሪኩን ደጋግመን እናስታውሰዋለን።

ከታዋቂው የታሪክ ጸሐፊ ጳውሎስ ኞኞ «አጤ ምኒልክ» መጽሐፍ፣ ከተክለጻድቅ መኩሪያ «አፄ ምኒሊክና የኢትዮጵያ አንድነት» መጽሐፍ፣ ከተለያዩ ድረ ገጾች እና የመገናኛ ብዙኃን ባገኘናቸው መረጃዎች የዚህ ሳምንት ክስተት የሆነውን ዓድዋ እናስታውሳለን።

ሴራው የሚጀምረው ከዓድዋ ጦርነት 12 ዓመታት በፊት በፈረንጆቹ የዘመን ቀመር 1884 ነው። የአውሮፓ አገሮች በርሊን ላይ ባደረጉት ስብሰባ አፍሪካን ለመቀራመት ሲወስኑ የጣሊያን ድርሻ ኢትዮጵያ ሆነች። ዳሩ ግን ያሰቡት ሊሳካ አልቻለም።

ኢትዮጵያ በቅድመ ዓድዋ ከወራሪዎችና ከኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር ተዋግታም ድል አድርጋለች። ከእነዚህም አንዱ በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት 1879 ዓ.ም ዶግዓሊ ላይ በራስ አሉላ አባነጋ አዝማችነት በጣሊያን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀዳጀችው ድል ነበር። በዚህም የጣሊያን ወታደሮች ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፉ በአሉላ አባ ነጋ ዶግዓሊ ላይ ዶግ አመድ ሆነዋል።

በጦርነቱ እንደማይሳካላት የገመተችው ጣሊያን እንደገና ደግሞ ውል ማጭበርበር አሰበች። በመሆኑም ለዓድዋ ጦርነት ምክንያት የሆነው የውጫሌው ውል፤በአንቀጽ 17 በጣሊያንኛ ትርጉሙ ኢትዮጵያ የጣሊያን ጥብቅ ግዛት ነች። የውጭ ግንኙነቷም በጣሊያን በኩል ይሆናል የሚለው ሐረግ መዘዝ አመጣ። በዚች አንቀጽ ምክንያት ጦርነቱ የማይቀር መሆኑ ተረጋገጠና ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ለጦርነቱ የአገራቸውን ሕዝብ «ክተት» ጠሩ።

«አሁንም አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል። በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም። ያገሬ ሰው፣ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘን እርዳኝ፤ ........» የሚለውን አዋጅ ተናገሩ።

ኢትዮጵያውያንም የእርስ በእርስ ግጭታቸውን፣ ውስጣዊ ችግሮቻቸውንና አለመግባባታቸውን ወደጎን ትተው፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ተጠራርተው እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መስካሪ ሆነው የመሪያቸውን ጥሪ ተከትለው ወደ ጦር አውድማው ተመሙ።

የዓድዋ ድል 100ኛ ዓመት መታሰቢያ ሲከበር፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታተመ የጥናት መድበል ላይ እንደተጻፈው፤ የጦርነቱ አዝማቾች፤ ዳግማዊ አፄ ምኒሊክና እቴጌ ጣይቱ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ አባነጋ፣ ራስ መኰንን፣ ራስ ሚካኤል፣ ራስ ወሌ፣ ራስ ስብሐት፣ ደጃዝማች ሐጎስ ተፈሪ፣ ራስ አባተ፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ) እና ዋግ ሹም ጓንጉል ናቸው።

እውቁ የታሪክ ጸሐፊው ተክለ ጻድቅ መኩሪያ እንደሚነግሩን፤ የኢትዮጵያ ተዋጊዎች የጣሊያንን ወታደር ከበው እየተፏከሩ በጥይትና በጎራዴ ሲደበድቡት የኢጣሊያ ጦር አራት ሰዓት ከተዋጋ በኋላ ሸሽት ጀመረ። በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያውያን እየተከታተሉ ሲወጉት፣ ጦር አዝማቹ ጄኔራል አልቤርቶኒ ተቀምጦበት የነበረው በቅሎ ተመቶ ወደቀ። ወዲያው ተነሥቼ አመልጣለሁ ብሎ ለመነሣት ሲጥር ከቅምጡ ሳይነሳ እየተሽቀዳደሙ የሚሮጡት ኢትዮጵያውያን ደርሰው ጄኔራሉን ማረኩት። የአንደኛው ክፍለ ጦር አዛዡ ተማርኮ፣ ሠራዊቱ በጭራሽ ከጠፋ በኋላ ሁለተኛው ክፍል የጦር ሠራዊት «ራአዮ» ከሚባለው ስፍራ ላይ ሆኖ፣ ካራት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የሦስተኛውን ክፍል የጄኔራል ኤሌናን ጦር ጨምሮ ተዋግቶ በመጨረሻ የጦር አዛዡ ጄኔራል አሪሞንዲ እዚያው ጦርነቱ ላይ ሞቶ ተገኘ።

ከዚህም በኋላ፤ በመጨረሻ ያለው የጣሊያን ጦር በተለይ ማርያም ሸዊቶ ከሚባለው ስፍራ ላይ ተጋጥሞ ከቀድሞው የበለጠ ጦርነት ተደረገ። ይልቁንም የመጨረሻው ድል የሚፈጸምበት በመሆኑ የሁለቱም የጦር ሠራዊት ተደባልቆ በጨበጣ በሚዋጉበት ጊዜ፣ በጨበጣ በሚደረገው ዘመቻ ከኢጣሊያኖች ይልቅ ኢትዮጵያውያን በጎራዴ አሰነዛዘር ቀልጣፎች ነበሩ።

ይሁን እንጂ ጣሊያኖች ተስፋ በቆረጠ ኃይል እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ በጉብዝና ሲዋጉ በመጨረሻ አዛዣቸው ጄኔራል ዳቦርሚዳ በጥይት ደረቱን ተመቶ ሞተ።

የጳውሎስ ኞኞ «አጤ ምኒሊክ» መጽሐፍ በወቅቱ የነበረውን ክስተት እንዲህ ይተርከዋል።

«የተተከለው ድንኳን ሲታይ ከብዛቱ የተነሳ አፍሪካ አውሮፓን ለመጠራረግ የተነሳች ይመስላል። የጦርነቱ ዕለት ኢትዮጵያውያኑ ደማቅ ቀለም ያለው ካባ ለብሰው፣ ጠመንጃና ጦር ይዘው፣ ጎራዴ ታጥቀው፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ለብሰው፣ አዝማሪዎቹ እየዘፈኑ ቄሶች፣ ልጆች፣ ሴቶች ሳይቀሩ ፀሐይዋ ፈንጠቅ ስትል በተራራው ላይ በታዩ ጊዜ የጣሊያንን ጦር አሸበሩት»

በወቅቱ በአስራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የነበሩት ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም በዓድዋው የጦር ግንባር በመሰለፍ ያስተዋሉትን «አውቶ ባዮግራፊ» በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲህ ጽፈውታል።

«የሰው ብዛት እንደ ጎርፍ ሆነ። እግረኞችም በቅሎኞችም ተደባልቀን እንርመሰመሳለን። ፈረሰኞች በጎን እያለፉን ይቀድማሉ። ይሮጣሉ! እንደተቻለን እንሽቀዳደማለን።

ጠመንጃ ሲንጣጣ ሰማን፣ መድፍ ወዲያው ያጓራ ጀመር። ተኩሱ እያደር እየባሰበት ተቃረበን፣ አረሮቹ ማፏጨት ጀመሩ። የቆሰሉ ሰዎች ተቀምጠው አገኘን። አያ ታደግ እጁን ተመትቶ ከመንገዱ ዳር ከዛፍ ሥር ተቀምጧል። ገና በሩቁ አይቶን ተጣራ፣ ቁስሉን በመቀነቱ አሰርንለት። ጥለነው እንዳንሄድ ለመነን፣ ፈይሣ ጠመንጃ የለውም፤ የቁስለኛውን ጠመንጃ ተሸከመና እዚያው ቀረ። እኔ ዝም ብዬ ወደ ግምባር አለፍኩ። የማውቀውን ሰው አንድም አላጋጠመኝም። ተኩስ ስለበዛ መሮጥ የማይቻል ሆነ። የሰውም ብዛት እንደልብ አያስኬድም።

ደጃዝማች ማናዬ እና ልጅ አስፋው ሁለቱም ቆስለው ድንጋይ ተንተርሰው ተጋድመው አገኘኋቸው። ልጅ አስፋው (በኋላ ፊታውራሪ አስፋው) አወቀኝና ጠቀሰኝ። ዝም ብዬው እንዳላየ ሰው ወደ ግንባር ሮጥኩ። ጦራችን ተደባልቋል። ሰውና ሰው አይተዋወቅም። ሴቶች ገምቦ ውሃ እያዘሉ፣ በበቅሎዎቻቸው እንደተቀመጡ፣ ለቁስለኞች ውሃ ያቀርባሉ። ሲነጋገሩ ሰማኋቸው። «ኧረ በጣይቱ ሞት» ይላሉ። እቴጌ የላኳቸው ይሆናሉ እያልኩ አሰብኩ።

ነጋሪቱ ከግምባርም፣ ከጀርባም፣ ከቀኝም ከግራም ይጎሸማል። የተማረኩ ጣሊያኖችን አየሁ። ወዲያው ምርኮኞቹ በዙ፣ አንዳንዶቹ ወታደሮች፣ ይበልጡን ጣሊያኖችን እየነዱ መጡ። በኋላ የምርኮኞች ብዛት ለዓይን የሚያሰለች ሆነ፤ ድል ማድረጋችንን አወቅሁ። ጣሊያኖች መዋጋታቸውን ትተው ማርኩን እያሉ ይለምናሉ። እንደዚህ የዓድዋ ጦርነት ዕለት አንድ ጥይት እንኳ ሳልተኩስ ጦርነቱ አለቀ። »

በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ የዓድዋ ጦርነት የተጠናቀቀው፤ ክብር ለጀግኖቻችን እና ታሪክን ሰንደው ላቆዩልን ጸሐፊዎች!

### የካራማራ ድል

ሌላኛው የዚሁ የየካቲር ወር ድል ደግሞ በዛሬዋ ቀን የካቲት 26 ቀን 1970 ዓ.ም የተፈጸመው የካራማራው ድል ነው።

ይሄኛውም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከወራሪ ራሳቸውን የተከላከሉበትና ነፃነታቸውን ያስጠበቁበት የድል በዓል ነው። በወቅቱ በዚያድ ባሬ ይመራ የነበረው ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት «ታላቋን ሶማሊያ እገነባለሁ» በሚል ሕልም የኢትዮጵያን መሬት ለመውረር አስቦ እሱም ልክ እንደ ጌቶቹ አውሮፓውያን ሽንፈትን ተከናንቦ የተመለሰ ነው።

ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም «ትግላችን ቅጽ ፩» መጽሐፍ እና የካራማራ ድል በተከበረባቸው ዓመታት ከተሠሩ ዘገባዎቻችንና ከተለያዩ ድረ ገጾች መረጃዎችን አሰባስበን በየዓመቱ የካቲት 26 የሚከበረውን የካራማራ ድል እናስታውሳለን።

ለወረራ አሰፍስፎ በመጣው የዚያድ ባሬ ጦር ከሐምሌ 1969 ዓ.ም እስከ የካቲት 1970 ዓ.ም ድረስ ምሥራቃዊዋ የኢትዮጵያ ክፍል ኦጋዴን ጦርነት ተካሄደባት። ሶማሊያን ለ21 ዓመታት የመራት ጄኔራል ዚያድ ባሬ ኦጋዴንን በመጠቅለል ታላቋን ሶማሊያ የመመሥረት የቆየ ራዕይ ነበረው። ጊዜ አይቶ ወቅትን ገምቶ ኢትዮጵያ በገንጣይ አስገንጣዮች ትግል የተዳከመች ሲመስለው እቅዱን ለማሳካት ጊዜው አሁን ነው አለ።

ዚያድ ባሬ ያሰበውን ዳር ለማድረስ የኢትዮጵያን ጠላቶች ተጠቀመ። ያዋጣኛል ያለውን የሴራ መንገድ ሁሉ ተከተለ። ሶማሊያ በ1969 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ ግልፅ ወረራ ከመፈፀሟ በፊት በህቡዕ በተደራጀ ቡድን ተደጋጋሚ ጥቃት በመሰንዘር የኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል ማዳከም የሴራው አካል ነበር። ጦርነቱ በግልፅ በታወጀበት በሐምሌ ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ሳምንታት የሶማሊያ ጦር ባልታሰበ መልኩ ጅግጅጋ፣ ሐረርና ድሬድዋ ድረስ ዘልቆ ገባ።

በመጀመሪያ በሶቭየት ኅብረት እና በመቀጠልም በአሜሪካ ድጋፍ የነበረው የፕሬዚዳንት ዚያድ ባሬ ጦር ለድል የተቃረበ መሰለ። የኋላ ኋላ የውጭ ድጋፍ እየቀነሰበት የመጣው የሶማሊያ ጦር የኢትዮጵያ የውስጥ ተገንጣይ ኃይሎች የውስጥ ለውስጥ ድጋፍ ስላልተለየው ጦርነቱን ከመግፋት አልተቆጠበም ነበር።

ልክ እንደ ዓድዋው በዚህን ጊዜም የኢትዮጵያው መሪ ለጀግና ሕዝባቸው የክተት ጥሪ አቀረቡ። ሚያዚያ 4 ቀን 1969 ዓ.ም በብሔራዊ ቴሌቪዥን ቀርበው ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የሚከተለውን የክተት ጥሪ አቀረቡ።

«...ታፍራና ተከብራ የኖረችው ኢትዮጵያ ተደፍራለች። ለብዙ ሺህ ዓመታት አስከብሮን የኖረው አኩሪ ታሪካችን በዚህ አብዮታዊ አዲስ ትውልድ ጊዜ መጉደፍ የለበትም። አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊት! የኢትዮጵያ ሕዝብ! ለክብርህና ነፃነትህን ለመድፈር ሀገርህን ለመቁረስ የተጀመረው ጣልቃ ገብነትና ወረራ ከመለዮ ለባሹ ጋር ተሰልፈህ ለመደምሰስ የምትዘጋጅበት ጊዜ አሁን ነው። ተነስ! ታጠቅ! እናሸንፋለን!»

በተደረገለት ጥሪ የኢትዮጵያ ሕዝብም የአገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ቀፎው እንደተነካ ንብ በቁጣ ወጣ። የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጦር ወደ ፍፁሜያዊ ማጥቃት እና እልህ አስጨራሽ ጦርነት መግባቱን የሚያመላክቱ እርምጃዎች መታየት ጀመሩ። ከኦጋዴን ሞቃታማ ቦታዎች በአንዱ «ካራማራ» ከሚባለው ተራራ ከምድርም ከሰማይም እሳት የሚተፉ የኢትዮጵያ ወታደር የጦር አረሮች ምድሪቱን ዘነቡባት።

ታላቋን ሶማሊያ የመመሥረት ሕልም አንግቦ የነበረው የዚያድ ባሬ ጦር አይቀጡ ቅጣት ተቀጣ። ኢትዮጵያ በታሪክ እንደለመደችው አሁንም ድል አደረገች።

የካቲት 26 ቀን 1970 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጦር፣ የእናት ሀገር ወዶ ዘማቾች እና 16 ሺህ የሚደርሱ የፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮዋ ኩባ ሀገር ወታደሮች ይህን ታሪካዊ ጦር ተቀላቅለው የዚያድ ባሬን ጦር ድባቅ መትተው የኢትዮጵያን አሸናፊነት ታወጀ።

በመጽሐፋቸው ላይ ባስቀመጡት በአንዲት የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ገጠመኝ እንሰናበት። በኩባ እና በሌሎች ወዳጅ ሀገራት አማካኝነት ኮሎኔል መንግሥቱ እና ዚያድ ባሬ ለውይይት ተጠርተው በየመን ይገናኛሉ። ዚያድ ባሬ እብሪተኛ ስለሆነ ኮሎኔል መንግሥቱ የእብሪት መልስ እንዳይመልሱ በወዳጆቻቸው ተመክረዋል።

የተፈራው አልቀረም በውይይቱ ላይ ዚያድ ባሬ ኮሎኔል መንግሥቱን «ጦርነት የት ታውቃለህና ነው! ጦርነት እንዴት እንደሆነ አሳይሃለሁ» ብሎ ፎከረ። ዳሩ ግን ኮሎኔል መንግሥቱም እብሪተኛ ነበሩና (መታገስ አልቻልኩም ነው የሚሉ እርሳቸው) ምክሩን ጥሰው «ማን ጦርነት እንደሚችል እንተያያለን! እዚያው እንገናኝ!» ብለው ፎከሩ። ውይይቱም ያለ ስምምነት ተቋጨ።

**እነሆ ጦርነት ማን እንደሚችል ታየ! ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም አሸናፊ ናቸው!**

ስፖርት እና መዝናኛ


# የዝነኞች ገጽ

# ሰላዩ፤ የዓድዋ ድግስ አሰናባሪ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**ጣሊያን ሞኙ.... የሀበሻን ልክ አያውቅማ...ባንዳ ሁሉ ባንዳ ይመስለዋል እንዴ?....አይሁዳዊው ይሁዳ ጌታውን ስሞ በሰላሳ ዲናር ሸጠው፤ ኢትዮጵያዊው ይሁዳ ግን ሀገራቸውን ለማዳን ሲሉ የጄኔራሉን ጉልበት ስመው ሄዱ...የኢትዮጵያን አርበኛ አበላለሁ ብሎ የሞት ድግስ ደገሰ አሉ....የማን ዘር ጎመን ዘር!.... አሰናባሪው ባሻ አውአሎምስ የሀበሻ ልጅ አይደሉ... ...ከጮማውም፣ከቀዩም፣ከሸንጡም፣ከሻኛውም እየቆረጡ፤ ከጠላውም፣ከጠጁም እየቀዱ በአናት በአናቱ አስጋፉት.... ደጋሹ ጣሊያንም በስካርና በቁንጣን ፈንድቶ በራሱ ድግስ ሞተ... ባሻ አውአሎም የዘረጉትን የመረጃ ሰንሰለት፣ ጣሊያኖቹ በራሳቸው አንገት አጠለቁትና እንደ አንበሳ ገብተው እንደ ውሻ ተጎትተው ወጡ...**

በጦርነት ውስጥ የጠላትን መረጃ ማግኘት የአሸናፊነቱን ቁልፍ ለመጨበጥ ግማሹን መንገድ እንደሚሄድ ይቆጠራል። ያውም በዛኛው ዘመን ደግሞ በቃላቶች ብቻ ተገልጾ የሚታለፍ አይደለም። ምንም አይነት ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴ እንኳን በሌለበት በዚያ ዘመን በድፍረት ከጠላት መንደር ሰርስሮ መግባትና ገብቶም መረጃውን ይዞ በተሳካ መንገድ ለመውጣት ምናልባትም ባሻ አውአሎምን መሆን ይጠይቃል። ለመሆኑ ባሻ አውአሎም ማናቸው? የሠሩትስ ገድል ምንድነው? በዓድዋ ድል ማግስት የእኚህን ዝነኛ ሰላይ ገድል እንመልከት።



ባሻ አውአሎም በሞሳድና በሲአይኤ የስለላ ተቋማት ውስጥ የስለላን ጥበብ ተምረው የወጡ ምሑር ሰላይ አይደሉም። ይልቁንስ የኤርትራ ግዛት እንደዛሬው ከኢትዮጵያ እቅፍ ሳትወጣ በፊት በትግራይ ድንበር አካባቢ ተወልደው ያደጉና በፋሽስት ወረራ ወቅት፣ በነበራቸው ልዩ የስለላ ብቃት የፋሽስቱን ጦር ከአፈር ለመቀላቀል በስለላ ጀልባ ላይ እየቀዘፉ፣ ከፋሽስት መንደር ወደ አርበኛው፣ ከአርበኛው ወደ ፋሽስቱ መንደር ከማዶ ማዶ ሽርጉድ ሲሉ የነበሩ ድንቅ አሰናባሪ ሰላይ ናቸው። ታሪክ ዘነጋቸው እንጂ የስለላን ምንነት ሳያውቁ ተፈጥሮ በሰጠቻቸው እውቀት ብቻ የሠሩት ሥራ ዛሬ ዓለማችን ላይ ከሚወራላቸው ታላላቅ ሰላዮች ከሠሩት ቢበልጥ እንጂ አያንስም። በሀገራዊ ወኔና ፍቅር ብቻ ተነሳስተው የጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት ለሆነው የዓድዋ ድል ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በግራም ነፈስ በቀኝ ግን በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ እና የፋሽስት ጣሊያን ጦርነት ባሻ አውአሎምን ታሪካዊ ሰላይና የሀገር ባለውለታ አድርጓቸዋል። ቀደም ሲል ባሻ አውአሎም የራስ አርአያ ጀግና ወታደር የነበሩ ሲሆን፣ ራስ አርአያ ሲሞቱም የራስ መንገሻ ወታደር ሆኑ። ባሻ የሚለውንም ማዕረግ የሰጧቸው ራስ መንገሻ ነበሩ። ለሠሩት ታሪካዊ ሥራ ግን በትውልዶች ሳይዘመርላቸውና በቅጡ ሳይወራላቸው ኖረዋል።

ባሻ አውአሎም የሠሩት ገድል ምናልባት ከአንድ የጦር ጀኔራል የሚስተካከል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለመሆኑ ባሻ አውአሎም የሠሩት ትልቅ ገድል ምንድነው? ጊዜው ለየካቲት 23/1888ዓ/ም ተቃርቧል። በወቅቱ ደግሞ የጣሊያኗ ፋሽስት ጦር ጄኔራሎች እየረገፉባት ስታፈራርቃቸው የነበረበት ጊዜ ነው። የዚያን ጊዜ ደግሞ ጦሩን የሚመራው ተረኛ ጄኔራል፣ ጄኔራል ባራቶሪ ነበር። ይህ ሰው እጅግ በጣም ብዙ የሚባሉ የኢትዮጵያ ሀገራቸውን ጡት ነካሽ ባንዳዎችን በየስርቻው አሰማርቶ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያዊ በላይ የሚያውቅ የለምና እየሰለሉ መረጃን እንዲያመጡለት አደረገ። እንዳለመታደል ሆኖ ደግሞ ሰላቶው ፋሽስት ለስለላ ከመረጣቸው መሐከል ባሻ አውአሎም አንደኛው ናቸው። ጄኔራሉም የስለላ መረቡን በመዘርጋት እጩዎቹን አሰማራቸው። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ አብዛኛዎቹ በጥቅማጥቅም ተታለው የእውነትም የኢትዮጵያን ጦር እየሰለሉ መረጃን ሲያቀብሉ ነበር። በተቃራኒው ደግሞ ባሻ አውአሎምና ጥቂት መሰሎቻቸው ደግሞ የባራቶሪ አሽከር ሆነው በመቅረብ ለእናት ሀገራቸው ቆሙ። ለሁሉም ምሳሌ መሆን የቻሉና ነጥረው በመውጣት ታምርን መስሥራት የቻሉት ግን ባሻ አውአሎም ነበሩ።

እናም የታላቁ ሰው ታምራዊ ጀብዱ ሲጀምርም እንዲህ ነበር። ጄኔራል ባራቶሪ የኢትዮጵያ አምላክ አይሁንልህ ሲለው ከሁሉም አብዝቶ የሚቀርበውና

**የስለላን ምንነት ሳያውቁ ተፈጥሮ በሰጠቻቸው እውቀት ብቻ የሠሩት ሥራ ዛሬ ዓለማችን ላይ ከሚወራላቸው ታላላቅ ሰላዮች ከሠሩት ቢበልጥ እንጂ አያንስም። በሀገራዊ ወኔና ፍቅር ብቻ ተነሳስተው የጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት ለሆነው የዓድዋ ድል ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል**

የሚያምነው ባሻ አውአሎምን ነበር። አስጠርቶም የመታነቂያ ገመዱን ከትልቅ የስለላ አደራ ጋር ሰጣቸው። ባሻም አይሆንም ሀገሬንማ አሳልፌ አልሰጥህም አላሉትም። ይልቁንስ ደስ አላቸው። ባራቶሪም ይሁዳ ጌታውን በሠላሳ ዲናር የሸጠበትን ታሪክ ሳያስታውስ አልቀረም። "የሰው ልጅ ለጥቅሙ ሲል ሰማያዊ ፈጣሪውን ከሸጠ ይሄ ድሃ ሀገሩን የማይሸጥበት ምን ምክንያት ሊኖር ይችላል" ሲል በልቡም የተሳለቀበት ይመስላል። ኢትዮጵያዊ ማን እንደሆን አያውቀውማ፣ ምን ያድርግ። እናም ከፊት ድሉን አሻግሮ እያየ አውአሎምን በፈገግታ ወደ ስለላው ሜዳ ሸኛቸው። አይሁዳዊው ይሁዳ ጌታውን ስሞ ሸጠው። ኢትዮጵያዊው ይሁዳ ግን ሀገራቸውን ከቀኝ ገዢው ለማስለቀቅ የባራቶሪን ጉልበት ስመው ሄዱ።

ከፋሽስቱ የጦር መንደር ወጥተውም ስለጉዳዩ እያሰላሰሉ ወደ አጼ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት አቀኑ። ከዚያም ደርሰው የገጠማቸውን ነገር ለንጉሡ ገለጹላቸው። አጼ ምኒሊክም ይህንን ነገር ከአውአሎም አንደበት ሰሙ። ከዙፋናቸው ብድግ ብለው ከወለሉ ላይ ጎርደድ ጎርደድ እያሉ በሀሳብ ባሕር መቅዘፍ ጀመሩ። ወዲያው ባለቤታቸውና የቀኝ እጃቸው የሆነችውን እቴጌ ጣይቱን አስጠሯት። አጼ ምኒሊክ፣ እቴጌ ጣይቱ እና ባሻ አውአሎም ለሦስት አንድ ድንገተኛ ታላቅ ስብሰባ ማካሄድ ጀመሩ። ባሻ አውአሎም ይዘውት በመጡት መረጃ ዙሪያ ብዙ መከሩ፣ አወጡ፣ አወረዱ በስተመጨረሻም አንድ ሀሳብ ከመሃከላቸው ዱብ አለ። የፋሽስቱ ጄኔራል የአጼ ምኒሊክን ዙፋን በመረከብ የኢትዮጵያን በእጁ ለማድረግ እጅጉን ስለቋመጠ። ትልቅ የሠርግ ድግስ ደግሶ የጥሪ ካርድ በታኙን ባሻ አውአሎምን በመጠባበቅ ላይ ነው። አጼ ምኒሊክም ጥሪ አክባሪ ናቸውና መቼም አክብሮ ለጠራቸው የጣሊያን ጦር ስለ ምላሹ ተማከሩበት። የምላሹንም ድግስ በምን አይነት መልኩ መሆን እንዳለበት ሦስቱም ከተማከሩ በኋላ አውአሎምም ሌላኛውን የሠርግ ምላሽ፣ የጥሪ ካርድ በልባቸው በመያዝ የአጼውን ቤተመንግሥት ቅጥር ግቢ ለቀው ዳግም ወደ ጄኔራሉ ባራቶሪ ተመለሱ።

ጄኔራሉ፣ ባሻ አውአሎም አንድ የምሥራች ይዘው እንደሚመጡ እርግጠኛ ሆኖ ነበር። በጉጉት እየጠበቃቸው የነበሩት አውአሎም ከባራቶሪ ዘንድ ደረሱ። በኩራትም ጠጋ ብለው ደስ የሚያሰኝ ጮማ ወሬ ይዘው እንደመጡ ገለጹለት። ይሄኔ ባራቶሪ በደስታ ጮቤ ረገጠ። ወሬውንም ለመስማት ተጣደፈ። 'እህሳ ባሻዬ በል ንገረኝ' አለ። ባሻ አውአሎም ያንን ትኩስ ጮማ ወሬ በቢላ እየቆረጡና በአዋዜ እያጠቀሱ ማጉረሱን ቀጠሉ። "ምን መሰለህ ጌታዬ የፊታችን እሁድ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚከበር አንድ በዓል አለ። እለቱ የጊዮርጊስ ታቦት የሚወጣበት ቀን ነው። እንደአጋጣሚ ሆኖ ደግሞ በዓሉ ከሰንበት ጋር ተገናኝቷል። ይህ ደግሞ ሌላ የማይገኝ እድል ነው። ከምንም በላይ ለፈጣሪያቸው ቅድሚያ ስለሚሰጡ በዚህ እለት ላይ ጦር ማንሳት ይቅርና ሥራ እንኳን አይሠሩም። በመሆኑም ንጉሡና ከፊሉ ሠራዊቶቻቸው ለክብረ በዓሉ ይወጣሉ። የተቀሩትም ቢሆን ቀለብ ፍለጋ በየቦታው ይበተናሉ። ስለዚህ ያለምንም መንፈራገጥ ንጉሡን ማርከህ ሀገሪቱን በቁጥጥርህ ስር ማድረግ ትችላለህ። ታዲያ ከዚህ የተሻለ ጊዜና ቦታ ከየት ታገኛለህ ፍጠን እንጂ' በማለት አውአሎም ቀና ሲሉ፣ ከባራቶሪ ፊት ላይ ጸሐይን የሚያስንቅ ወገግታ ተመልክተው 'አዬዬ ጣሊያን ሞኙ ሰው አማኙ' ሲሉ በልባቸው ተረቱበት። ጄኔራሉ በጥርጣሬ ምንም ጊዜ ለማባከን አልፈለገም። ወዲያው ጦሩ ለ23ቱ የጊዮርጊስ እለት እንዲዘጋጁ አዘዘ።

በሠርጉ ደጋሽ የፋሽስቱ ጦር እና በጥሪ አክባሪው የኢትዮጵያ አርበኛ በጉጉት ስትጠበቅ የነበረችው የካቲት 23 ቀን ደረሰች። ለዚህች እለት ሽር ጉድ ሲል የከረመው የባራቶሪ ጦር ወፎች ሳይንጫጩ ገና በማለዳው ዘመናዊ ጦሩንና ጓዙን ሸክፎ ተሰናዳ። አሁን የቀረው ብቸኛው ነገር ቢኖር የጄኔራላቸው ፊሽካ ብቻ ነው። ምሽቱ አልነጋልህ ብሎት ያለ እንቅልፍ ያደረው ጄኔራሉም የጦር ሜዳ ካባ ጥሩሩን ለብሶ ተነሳ። ሙሽሪቱን ኢትዮጵያን የራሱ ለማድረግ በልቡ እየቸኮለ 'በሉ እንግዲህ እንሂድ' አለ። በሰላቶ ጀሌዎቹም ታጅቦ በሚሠራው ጀቡዱ ከፋሽስት መንግሥት ስለሚቸረው ክብርና ዝና እያሰበ ጉዞውን ጀመረ። ባሻም በልባቸው ከት ብለው እየሳቁ የመስዋዕቱን በግ እየነዱ ወደ ዓድዋ ተራሮች ይዘዋቸው ወጡ።

በሌላ በኩል ደግሞ ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ከዓድዋው የድግስ ስፍራ ላይ ድብቅ ድንኳኑን ጥሎ በመመሸግ ሠርገኛውን የፋሽስት ጦር በመጠባበቅ ላይ ነበር። ሳሩን እንጂ ገደሉን መመልከት የተሳነው ፋሽስቱም ዘመናዊ የጦር መሣሪያውን እያንጓዘዘ፣ ሲነዳ መጣ። ጀግናው ባሻ አውሎአም ልክ ከሠርጉ ደጅ ላይ መድረሳቸውን ሲያዩ ድንገት በሚያስበረግግ ድምጽ 'ዘራፍ' አሉና ጎራዴያቸውን መዘው አጠገባቸው የነበረውን ሰላቶ እንካ ቅመስ አሉት። ይሄኔ አንድ.. ሁለት..ሶስት..እያሉ ለቁጥር የሚያዳግቱ የኢትዮጵያ አርበኛ ሠራዊት ከየት መጡ ሳይባል፣ ከሰማይ የወረዱ እስኪመስል ድረስ ከመሸጉበት ጎሬ እየወጡ የፋሽስት ጣሊያንን ጦር እንደጉንዳን ሰፈሩበት። ያንን ሁሉ ዘመናዊ የጦር መሣሪያና መድፍ ተሸክሞ የመጣው የባራቶሪ ጦር መላቅጡ ጠፍቶት ተርበደበደ። ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ የፋሽስቱን አንገት እየቀላ ከላዩ ላይ ቁጭ ብሎ ከወዲህ ይሸልላል፣ ይፎክራል፣ ከወዲያ ቀረሮቶውን እየነፋ ሲያሻው በፈረስ ይጋልብበታል። አንዴ ህልም፣ ሌላ ጊዜ እብደት ሲመስላቸው በግራ መጋባት የናወዙት ባራቶሪና ጦሩ የሚያደርጉትን ቢያጡ የያዙትን መሣሪያ ዛፍ ይሁን ሰው ብቻ ባገኙት ነገር ላይ ሁሉ ያንዠቀዥቁት ጀመሩ። ወይ ፍንክች ሀበሻን አያውቁትም ኖሯል። የዘመናዊው መሣሪያ የተኩስ እሩምታ መች ሊያስፈራው፤ አጥንቱ ከመሣሪያው ብረት የጠነከረ፣ ደሙም ከመድፉ እሳት የባሰ የሚያቃጥል መሆኑን አልተረዳም። እራሱ በደገሰው ድግስ ጥሪ አክባሪው የኢትዮጵያ አርበኛ ከስፍራው ተገኝቶ ሠርግና ምላሹን አንድ አደረገው። ድል ያለውን የጣሊያንን ድግስ፣ ድል ባለ ሽንፈት አሸገው ስጦታውን ለፋሽስቱ መንግሥት ላኩለት። የድግሱ አሰናባሪ የነበሩት ጀግናው ሰላይ ባሻ አውአሎምም የሰላቶውን አንገት እየቀሉ በሸለላና ፉከራው ቢደክሙም፣ ነገር ግን ምንም ሳይሆኑ ከጦርነቱ ተርፈው በሰላም ተመለሱ። ለሰሩት ገድልም ንጉሡ አጼ ምኒሊክ የእንጥጮ ወረዳ ግዛትን እንዲያስተዳድሩ በሽልማት መልክ ሰጧቸው። የጥቋቁር ወርቆች ደማቅ ታሪክም በዓለም ሁሉ እየዞረ እጅን በአፍ አስጫነ። ይሄው ዛሬም በኩራት 'ዓድዋ' እንላለን። ትላንት፣ ዛሬ፣ ነገም፣ ሁሌም ዓድዋ!!!

# ዓለም አቀፍ



## በኮሎምቢያ ታግተው የነበሩ የፖሊስ አባላት ተለቀቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኮሎምቢያ ደቡባዊ ካኬታ ግዛት በነበረው የተቃውሞ ሰልፎች ታግተው የነበሩ የፖሊስ አባላት እና የነዳጅ ማውጫ ሠራተኞች ነጻ መውጣታቸውን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ፔትሮ ተናገሩ።

ባለፈው ሐሙስ የነዳጅ አውጭው ኩባንያ፣ ኤመራልድ ኢነርጂ ግቢ በነዋሪዎች ከተዘጋ በኋላ ብጥብጥ ተቀስቅሷል።

ነዳጅ በሚወጣበት አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች መንገዶችን እንዲሠራ ኩባንያውን እየጠየቁ እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

የኮሎምቢያ ፕሬዚዳንት ጉስታቮ ፔትሮ የታገቱት 79 ፖሊሶች እና ዘጠኝ የነዳጅ ማውጫ ሠራተኞች እንዲለቀቁም ጠይቀው ነበር።

በተነሳው አለመረጋጋት አንድ የፖሊስ አባል እና ሰላማዊ ሰው ተገድለዋል።

የታገቱት የፖሊስ አባላትና ሠራተኞች መለቀቅን በተናገሩበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ ለሁለቱ ግለሰቦች ሞት ተጠያቂነት እንዲሰፍን ምርመራ እንዲጀመር አዘዋል።

የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ አልፎንሶ ፕራዳ፣ቀደም ብለው ግለሰቦቹ በጥይት መገደላቸውን ተናግረዋል።

አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች የአገሪቱ ቀደምት ሕዝቦች ሲሆኑ ኤመራልድ ኤነርጂ ነዳጅ በሚያወጣበት ሳን ቪሴንቴ ዴል ካጓን የመንገድ መሠረተ ልማት እንዲዘረጋም ጠይቀዋል።

የነዳጅ ኩባንያው በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ የሮይተርስ የዜና ወኪል ቢጠይቀውም ምላሽ ከመስጠት ተቆጥቧል።

የኮሎምቢያ ፖሊስ በግጭቱ ለተገደለው ሪካርዶ ሞንሮይ ለተሰኘው ፖሊስም በትዊተር ገጹ ኃዘኑን ገልጿል።

“ዛሬ ከምንጊዜውም በበለጠ አንድነታችን ተጠናክሯል” በማለት ፖሊስ በትዊተር ገጹ መልዕክት ያስተላለፈ ሲሆን “ሪካርዶ ለሙያው ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል” ብሏል።

በስፍራው የአሸማጋይነት ሚና ነበረው የተባለው የኮሎምቢያ የሰብዓዊ መብት እንባ ጠባቂ ሠራተኛ ካርሎስ ካማርጎ ተቃዋሚዎችን በማነጋገር በኩባንያው ላይ የቤንዚን ቦምቦችን እንዳይወረውሩ እንዳሳመኗቸው ተናግረዋል።

በኮሎምቢያ ውስጥ በነዳጅ እና በማዕድን ማውጫዎች አቅራቢያ ባሉ አካባቢዎች ያሉ ተቃውሞዎች የተለመዱ ናቸው።

የአካባቢው ነዋሪዎች እነዚህ ኩባንያዎች መንገዶችን እና ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ መሠረተ ልማት እንዲገነቡም በተደጋጋሚ ሲጠይቁም ይሰማሉ።

ፖሊስ በበኩሉ በአውሮፓውያኑ 2016 የነበረውን የሰላም ስምምነት ያልተቀበለው የፋርክ አማጽያን ንዑስ ቡድን በግዛቱ ውስጥ እንደሚገኝ እና ከዚህ ግጭት ጀርባ ሊኖር ይችላልም ብሏል።

ከዚህ በተለየ ፕሬዚዳንት ፔትሮ ባልተጠበቀ ሁኔታ የአገሪቱ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በራሳቸው ልጅ እና ወንድማቸው ላይ የሙስና ወንጀል ምርመራ እንዲከፍት የሚጠይቅ መግለጫ በትዊተር ገጻቸው አውጥተዋል።

መግለጫቸው በትልቁ ልጃቸው ኒኮላስ ፔትሮ ቡርጎስ እና ወንድማቸው ሁዋን ፈርናንዶ ፔትሮ ኡሬጎ ላይ ስለቀረበው ክስ በዝርዝር አልገለጸም።

## ቤላሩስ በኖቤል ሽልማት አሸናፊው ላይ የ10 ዓመት እስር ፈረደች

በጋዜጣው ሪፖርተር



የቤላሩስ ፍርድ ቤት በኖቤል ሽልማት አሸናፊው አሌስ ቢያሊያስኪን ላይ የአስር ዓመት እስር ፈረደበት።

የሕዝብን ጸጥታ በሚጥሱ ድርጊቶች ላይ ገንዘብ በማዘዋወርና ድጋፍ በማድረግም ጥፋተኛ እንደተባለ የቪያስና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አስታውቋል።

የኖቤል አሸናፊው ደጋፊዎች በበኩላቸው ጨቋኝ የሆነው የቤላሩስ መሪ አሌክሳንደር ሉካሼንኮ አገዛዝ ዝም ሊያሰኘው እየሞከረ ነው በማለት ተችተዋል።

አሌስ ቢያሊያስኪ በአውሮፓውያኑ 2022 የኖቤል የሰላም ሽልማት ካገኙ ሦስት አሸናፊዎች አንዱ ነው።

በቤላሩስ በነበረው አወዛጋቢ ምርጫ ተጭበርብሯል በሚል በርካቶች በአደባባይ ተቃውሞ ማድረጋቸውን ተከትሎም ነው አሌስ ከሁለት ዓመት በፊት ለእስር የተዳረገው።

የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ ገንዘብ ወደ ቤላሩስ እያሻገረ ነው በሚልም ነበር የተከሰሰው።

የአውሮፓውያኑ 2020 የምርጫ ውጤት ለተቃወሙ ሰላማዊ ሰልፈኞች ፖሊስ የጭካኔ ምላሽ መስጠቱ የተገለጸ ሲሆን በርካታ የፕሬዚዳንቱ ተቺዎችም ታስረዋል።

አሌስ ከሁለት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ቫለንቲን ስቴፋኖቪች እና ቭላድሚር ላብኮቪች ጋር ነበር በፍርድ ቤት የቀረበው።

ስቴፋኖቪች የዘጠኝ ዓመት እስር ሲፈረድበት፣ ላብኮቪች ደግሞ ሰባት ዓመት እንደተፈረደበት በአውሮፓውያኑ 1996 በአሌስ የተቋቋመው ቪያስና የሰብዓዊ መብት ድርጅት አስታውቋል።

ሦስቱም ጥፋተኛ አይደለንም ሲሉም ለፍርድ ቤቱ ቃላቸውን ሰጥተዋል።

የአሌስ ባለቤት ችሎቱ “የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ሥራቸውን የተቃረነ ነው” እንዲሁም ብያኔው “ጭካኔ የተሞላበት” ስትል ገልጻዋለች።

ለእስር ከተዳረገበት ጊዜ ጀምሮ ባለቤቷ ከእስር ቤት የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በመጥቀስ “ሁልጊዜም ደህና እንደሆነ፣ ሁሉ ነገር ጥሩ ነው ይላል። ስለ ጤንነቱ ምንም አያማርርም። እኔን ላለማበሳጨት ይሞክራል” ብላለች።

የቪያስና ቃለ አቀባይ ኮስትያ ስታርዱቤትስ በበኩላቸው በሦስቱ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ላይ የተላለፈው የፍርድ ውሳኔ “ ልብ የሚሰብር ነው” ብለዋል።

የኖቤል የሰላም ሽልማትን ሰጪው ተቋም የኖርዌይ የኖቤል ኮሚቴ ሰብሳቢ ቤሪት ሪስ-አንደርሰን በበኩላቸው በአሌስ ላይ የተወሰነው ፍርድ አሳዛኝ ነው ፤እንዲሁም ክሱም ፖለቲካዊ ነው ሲሉም ተችተዋል።

አሌስ በቤላሩስ ውስጥ አንጋፋ የሚባል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ነው።

በአውሮፓውያኑ 1996 እስካሁን ቤላሩስን የሚመሯት ፕሬዚዳንት ሉካሼንኮን የተቃወሙ ሰዎች ላይ በደረሰው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃም ነበር የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቱን ያቋቋመው።

በአውሮፓውያኑ 2011 በግብር ማጭበርበር ክስ ለሦስት ዓመታት ታስሯል።


## የውጪ ኦዲት አገልግሎት ጨረታ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ሰዋስወ ገነት ልማትና ተራድኦ ድርጅት የ2022 በጀት አመት ሂሳቡን በውጪ ኢዲተሮች አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን የምታሟሉ ኦዲተሮች እንድትወዳደሩ እንጋብዛለን፡፡

• ተፈላጊ መስፈርት፡-

1.የ2014 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያለው

2.የዘመኑን ግብር የከፈለና በቂ ባለሙያ ማሰማራት የሚችል

3.ሲፕኤ/ኤሲሲኤ የተግባር ሰርተፍኬት ያለው

4.የሙያ ፈቃድ ያለው

5.በኢንተርናሽናል ወይም ሐገር በቀል መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ተመሳሳይ አገልግሎት በመስጠት የ 5 ዓመት ልምድ ያለው ከዚህ በላይ ያለውን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች አዲስ አበባ በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤታችን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በ5(አምስት)የስራ ቀናት ውስጥ በስራ ሰዓት ከጧቱ 2፡30 እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ መጥታችሁ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ማሳሰቢያ፡-የጨረታ ሰነዶቻችሁን በታሸገ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባችኋል፡፡

አድራሻ፡- ራት ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ወረድ ብሎ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት ገባ ብሎ

ስልክ፡-0911472865

**ሰዋስወ ገነት የልማትና ተራድኦ ድርጅት**



## INVITATION TO BID
### OPEN NATIONAL COMPETITIVE BIDDING
### Tender No. LP/OT/13/SIG/2015

1. Ethiopian Sugar Industry Group invites sealed bids from interested eligible & qualified national bidders for Construction of Maintenance work of Phillips Building.
2. A complete set of bidding document can be obtained during office hours from the address mentioned below upon payment of a non-refundable fee of Eth. Birr 300.00 (Birr Three Hundred) and presentation of 2015 E.C Trade license, TIN, VAT Registration, Current Tax Clearance & Suppliers' Registration Certificates from the concerned public body.

**Ethiopian Sugar Industry Group**
Procurement and Property Management Department
Kasanches, near Development Bank of Ethiopia,
Ki-med University College plc Building, 2nd Building 4th Floor Room No. 402
Josef Tito Street
Tel: 0115-500569, 0115-524589
P.O. Box 20034-1000
**Addis Ababa, Ethiopia**

3. Sealed bid marked as described in the bidding document and addressed to the above address must be received by the Group before 2:00 PM local time on March 21, 2023. The document will be received through bid box or hand delivered. No liability will be accepted by the buyer for loss or late delivery.
4. Bids will be opened in the presence of bidders or their representatives who choose to attend on the above mentioned date and address specified above at 2:30 PM local time in the Group Head office's Conference Hall.
5. All bid must be accompanied by a bid security Birr 50,000.00 (Fifty Thousand Birr). The bid security shall be in the original form of CPO or Unconditional Bank Guarantee from any Commercial Bank in Ethiopia. The Bid Security shall be valid for at least Ninty (90) days after the bid submission deadline. The bid shall remain valid for Sixty (60) days after the bid submission deadline.
6. Ethiopian Sugar Industry Group reserves the right to accept or reject any or all bids.

**Ethiopian Sugar Industry Group**

# ስፖርት





## ፈር ቀዳጇ የማራቶን ኮከብ


**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ በብዙ ነገሮች ከዓለምና ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆኗ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይነሳል። ቀዳሚ ካደረጓት መካከል በተለያዩ ዘርፎች አይረሴ ጀግኖቿ የፈፀሟቸው ገድሎችና የፃፏቸው ወርቃማ ታሪኮች ትልቅ ቦታ አላቸው። ለዚህም ብርቅዬ አትሌቶቿ ኦሊምፒክን በመሳሰሉ ታላላቅ የስፖርት መድረኮች ያስመዘገቧቸው አይረሴ ድሎች በብዙ አጋጣሚዎች ከዓለምና ከአፍሪካ የመጀመሪያዋ ሀገር ሆና ስሟ በታሪክ ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ችለዋል።

በስፖርቱ ዓለም በተለይም በአትሌቲክስ የረጅም ርቀት ውድድሮች ኢትዮጵያ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በበለጠ ገናና ስም እንዲኖራት ያስቻሉ በርካታ ዕንቁ አትሌቶች ባለቤት ናት። ለዚህ ደግሞ እንደ ዘመናችን ሁሉም ነገር ተመቻችቶላቸው ሳይሆን ከባዶ ተነስተው ፋና ወጊ በመሆን ለአሁኖቹ ከዋክብት አትሌቶች ፈር የቀደዱ ባለታሪኮች የመሠረት ድንጋይ ናቸው።

እንደ ዕድል ሆኖ ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ማራቶን ታሪክ በወንዶች በጀግናውና ታሪካዊው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ አማካኝነት ወርቅ ያጠለቀች የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት አገር ብቻም ሳትሆን በኦሊምፒክ የሴቶች አስር ሺ ሜትር በኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ የወርቅ ሜዳሊያ የተጎናፀፈች የመጀመሪያዋ ሀገር ነች። የሁለቱ ጀግኖች ዘመን የማይሽረው ገድል ዓለም ሁሌም የማይረሳው ኢትዮጵያውያንም ዘወትር የሚኮሩበት ሕያው ታሪክ ነው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በኦሊምፒክ መድረክ የመጀመሪያ የሆኑበት ታሪክ ግን ይህ ብቻ አይደለም። ሌላም ተጨማሪ የሆኑ በርካታ ገድሎች አሉ።

በዛሬው የስፖርት ማሕደር አምዳችንም ኢትዮጵያን



ከአፍሪካ የመጀመሪያዋ ያስባላትን ታሪክ በኦሊምፒክ ስለፈፀመችውና ብዙም ስለእሷ ሲነገር የማይስተዋለውን ፈር ቀዳጅ የማራቶን ጀግኒት ይዳስሳል። ይህች ታሪካዊ ኮከብ የማይረሳ አኩሪ ገድል በኦሊምፒክ መድረክ ብትፈፅምም እምብዛም ወደ መገናኛ ብዙኃን ስትቀርብ አትታይም። ተደጋግሞ መነገር የሚገባው ታሪኳም በሚገባው ልክ ሲዘከር አይታይም። ይሁን እንጂ በቀደሙት ዓመታት የቴሌቪዥን የስፖርት ዝግጅት ሲጀምር ከሚታዩ ምስሎች መካከል እሷ አኩሪውን ታሪክ ስትጽፍ የሚያሳየው ተንቀሳቃሽ ምስል በብዙዎች ዘንድ ይታወሳል።

ይህች የማራቶን ባለ ታሪክ ፋጡማ ሮባ ስለመሆኗ መገመት አይከብድም። እኤአ በ1996 አትላንታ ኦሊምፒክ ላይ ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ በ10 ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ሲያስመዘግብ፣ በ10 ሺ ሜትር ሴቶች የነሐስ ሜዳሊያውን እንቁዋ አትሌት ጌጤ ዋሚ ስታጠልቅ በሴቶች ማራቶን ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ በታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የወርቅ ሜዳሊያ በማስመዝገብ ለአሁኖች የርቀቱ ፈርጦች ፈርቀዳጅ በመሆን መላውን የጥቁር ሕዝብ ጮቤ አስረግጣለች ።

ፋጡማ ትልቁን ታሪክ ለመሥራትና ለበርካታ አፍሪካውያን ሴት አትሌቶች ምሳሌና የይቻላል ምልክት ለመሆን ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፋለች። ከአትላንታ ኦሊምፒክ አንድ ዓመት በፊት 1995 እኤአ ስዊድን ላይ በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ሀገሯን ወክላ ተሳታፊ ብትሆንም 19 ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው። ይሁን እንጂ ይህ ጥሩ የማይባል ውጤት ትልቅ ታሪክ ከመሥራት ተስፋ አላስቆረጣትም። በቀጣይ ዓመት ኦሊምፒክን እንድትሳተፍ የሚያደርግ ድል በጣሊያን የሮም ማራቶን አሸንፋ ወደ አትላንታ በማቅናት አይረሴውንና ታሪካዊውን ድል ለማኖር በቅታለች።

ከአትላንታ ጣፋጭ የኦሊምፒክ ድል ቀጥሎ ባሉ ዓመታትም ከ1997 እስከ 1999 ድረስ በቦስተን ማራቶን ለሦስት ተከታታይ ዓመት በማሸነፍ ዛሬ ላይ መኖሪያዋን ካደረገችባት የአሜሪካ ስፖርት አፍቃሪዎች ዘንድ የማትረሳ ኮከብ ለመሆን በቃች። በዚህም የከተማው ሰው(የቦስተን) ነዋሪዎችም «our lady» የእኛ እመቤት እያለ ይጠሯታል።

የኦሊምፒክ ድሏ በኢትዮጵያና በአፍሪካ የሴቶች ማራቶን ቀዳሚ የሆነችውን የፋጡማን ታሪክ ለመድገም ኢትዮጵያ አሥራ ስድስት ዓመታትን ጠብቃለች። የፋጡማ የኦሊምፒክ ድል በማራቶን ከ16 ዓመት በኋላ ቲኪ ገላና እኤአ በ2012 ለንደን ኦሊምፒክ ላይ ደግማለች።

ዕንቁዋ አትሌት ለኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰለፈችው በ1988 እኤአ ላይ በግማሽ ማራቶን ውድድር በመሳተፍ ነበር። በሁለት የዓለም የግማሽ ማራቶን ሻምፒዮናዎች ላይም እስከ 10 ባለው ደረጃ ለመግባት በቅታለች። በ1994 እኤአ ላይ የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን በፓሪስ ማራቶን ላይ ስታደርግ በ19ኛ ደረጃ ነበር የጨረሰችው።

ከዚያ በኋላ የመጀመሪያ የማራቶን ድሏን ደግሞ በሞሮኮ ማራኬሽ ላይ ያስመዘገበች ሲሆን ከሁለት ወራት በኋላ በሮም ማራቶን በድጋሚ ለማሸነፍ በቅታለች። በ1996 እኤአ ላይ በአትላንታ በተካሄደው ኦሎምፒክ በኢትዮጵያ የማራቶን ቡድን ለመሰለፍ የበቃችው ከዚህ ውጤቷ በኋላ ነው። በወቅቱ የኦሊምፒክ ማራቶኑን 2:26:05 በሆነ ሰዓት አንደኛ በመሆን ስታጠናቅቅ የሩሲያዋ ቫለንቲና ይጎሮቫና ጃፓናዊቷ ዩኩ አርሞሪ 2ኛና 3ኛ ደረጃ አግኝተዋል።

ከአትላንታ ኦሊምፒክ በኋላ በቦስተን ማራቶን ከ1997 እስከ 1999 እኤአ ለሦስት ጊዜ አከታትላ ካሸነፈች በኋላም ፤ በ2000 እኤአ ላይ ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ በመጨረስ በውድድሩ ታሪክ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግባለች። በ2000 እኤአ ላይ በሲድኒ ኦሊምፒክ በማራቶን ውድድር 9ኛ ደረጃ ያገኘች ሲሆን፤ በ2001 እኤአ ላይ ደግሞ በኤድመንተን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና 13ኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃለች። በ2004 እኤአ ላይ በጃፓን የናጋኖ ማራቶንም አሸንፋለች።





## በልጆች ትምህርት ላይ የወላጆች ሚና

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ። ሳምንቱ እንዴት ነበር? ይህ ሳምንት የአፍሪካ ኩራት የጥቁር ሕዝቦች ድል የሆነው የዓድዋ ድል የተከበረበት ሳምንት ስለነበር ብዙ የሀገራችሁን የድል ታሪክ የተማራችሁበት እንደነበር እገምታለሁ። እናንተም ልክ እንደ ጥንት አባቶቻችን ሀገራችሁን የምታኮሩ እንቁ እንደምትሆኑ አምናለሁ። ምክንያቱም ጎበዝና ተሰጥዖ ያለው ተማሪ ሁሌም ለሃገሩ ኩራት መሆኑ አይቀርም። ልጆችዬ ዛሬ ያዘጋጀችሁት ጽሑፍ ወላጆቻችሁ ሊያነቡት የሚገባ ጽሑፍ ነው። ወላጆቻችሁ ይህንን ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ በትምህርታችሁ ዙሪያ ለናንተ የሚጠቅም ነገር ስለሚያደርጉ እንዲያነቡ ጋብዟቸው እሺ።

ትምህርት ለሰው ልጆች የአዕምሮ እድገት እና የማገናዘብ አቅም መጎልበት እጅግ ወሳኝ መሆኑ በተለያየ ጊዜ ሲነገር እንሰማለን። በእውቀት ያልተገነባና ምክንያታዊነትን ያልተላበሰ አዕምሮ ከሌሎች መግባባት ይቸግረዋል፤ አለፍ ሲልም ሀገር ሊጎዳ የሚችል ጠንቅ ይሆናል። የዛሬ ችግሮቻችንም ከዚህ እውነት የሚመዘዙ እንደሆኑ ማስተዋል አያዳግትም፡፤ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን ከሁሉ በፊት ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል።

ልጆች ሀገር ይረከባሉ ተብለው የሚጠበቁ የነገ ተስፋና ለብዙዎችን የብርሃን ጮራ የሚፈነጥቁ የንፁሕ አዕምሮ ባለቤት ናቸው። ይህ ንፁሕ አዕምሮ ደግሞ ከነጭ ወረቀት ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ነጭ ወረቀት በብዕራችን የፃፍንበትን ሁሉ ይቀበልና አጉልቶ ያሳየናል። ልጆችም እንዲሁ ያሳየናቸውን ያስተማርናቸውን እና የነገርናቸውን አጉልተው ያንፀባርቃሉ። ስለዚህ በእነዚህ ንፁሕ ሕፃናት አዕምሮ ላይ የምንፅፈውን ነገር በጥንቃቄ ማጤን



ይኖርብናል።

ወላጆች እንደወላጅ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ልጆች ይዘው የሚወለዱት ንፁሕ አዕምሮ ሁሉን ተቀባይ እንደመሆኑ የሚበጃቸውን መጥኖ ማቀበልና በትምህርታቸው ላይ ትኩረት ሰጥተው ዓላማ ያላቸው ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ብዙ ጊዜ ቤተሰብ የሀገር መሠረት ነው ሲባል እንሰማለን። ይህንን አባባል ከአባባልነቱ አለፍ ብለን ምን ማለት ነው የሚለውን ስንመረምር ግን አይታይም። ቤተሰብ ወደፊት ሀገርን የሚያስተዳድር መሪ፣ ለሀገሩ ዘብ የሚቆም ወታደር፣ ሕዝብን በቅንነት የሚያገለግል ባለሙያ የሚወጣበት ትልቅ ተቋም ነው።

ልጆች እንዲህ ዓይነት ተቋም ሆነው እንዲገነቡ ለማድረግ ደግሞ ቤተሰብ ዛሬ ላይ የሚሠራው የቤት ሥራ ትልቁን ስፍራ ይይዛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልጆች ለትምህርት ያላቸው አመለካከት እየቀነሰ፤ ትኩረት ሰጥተው ዓላማ አስቀምጠው ትምህርታቸውን ለመከታተል ያላቸው ፍላጎት እየተቀዛቀዘ መጥቷል። ከዚያም አለፍ ሲል ያላቸው በራስ መተማመን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠፋ በሌሎች ላይ ተደግፈው የሚኳዙ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ ጥገኞች ወደመሆኑ እየተሻገሩ እንመለከታለን።

ለዚህም የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት አንዱ ማሳያ ነው። እንደሀገር በአጠቃላይ ፈተናውን ለመውሰድ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት 985 ሺህ 354 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ፈተናውን የወሰዱት 896 ሺህ 520 ተማሪዎች ናቸው። 50 በመቶና ከዚያ በላይ በማምጣት ወደ ዩኒቨርሲቲዎች ለመግባት የሚያስችላቸውን ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ብዛት ግን 29 ሺህ 936 ነው። ከነዚህ ውስጥ 22 ሺህ 936ቱ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ሲሆኑ 6 ሺህ 973 ተማሪዎች ደግሞ የማኅበረሰብ ሳይንስ ተማሪዎች ናቸው።

ሙሉ የቀን ትምህርት የሚያስተምሩ 2ሺ959 ትምህርት ቤቶች በፈተናው የተካተቱ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንድ ሺህ 798 ትምህርት ቤቶች በአማካይ አንድ ተማሪ ለማሳለፍ ችለዋል። የተቀሩት አንድ ሺህ 161 ትምህርት ቤቶች ግን ምንም ተማሪዎችን ማሳላፍ ያልቻሉ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

የ12ኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ብሔራዊ ፈተና ከዚህ ቀደም ይሰጥ ከነበረበት የፈተና ሥርዓት በተለየ መልኩ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲዎች ቅጥር ግቢ በመግባት የፈተናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ እዚያው እንዲቆዩ መደረጉና ፈተናው በዩኒቨርሲቲ መምህራን መሰጠቱ ይታወሳል። ይህም በየግዜው የሚነሳውን የፈተና ስርቆትና የኩረጃ ችግሮችን ከማስቀረት አንፃር ከፍተኛ ለውጦች የተገኙበት ነበር። ነገር ግን ይህ ሃሳብ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ሲገለፅ ብዙ ተማሪዎች አንስተውት የነበረው የተቃውሞ ሀሳብ ልጆች ምን ያህል በራስ መተማመን እንዳነሳቸውና ኩረጃን መሠረታቸው አድርገው እንደሚያስቡ የሚያሳይ ነው።

በሀገራችን ያለው የትምህርት ጥራት ደረጃ፣ ለተማሪዎች የተሟላና ምቹ ትምህርት ቤቶችና የመማሪያ ክፍሎች እንዲሁም ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ሥርዓት አለመኖር ልጆች ለትምህርት ያላቸው አመለካከትና ትኩረት ሰጥቶ አለመማር እንዳለ ሆኖ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሠጡት ትኩረት ድጋፍም ከዚህ በማይተናነስ መልኩ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ልጆች ምን ያህል ለትምህርታቸው ትኩረት ሰጥተው እየተማሩ ነው መከታተልና ተገቢውን ደጋፍ መስጠት አስፈላጊ ነው። ከቤት ዩኒፎርም ለብሶ ከመውጣት ባሻገር ምን ያህል በትምህርታቸው ውጤታማ እየሆኑ ነው የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል። ልጆች በማንም ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ራሳቸውን ችለው ለፈተና እንዲቀርቡ ስነልቦናቸውን ማዳበር ትልቁ የወላጆች ኃላፊነት ነው።

የነገዋን ኢትዮጵያን በእውቀት ጎልብተው እንዲረከቡ ልጆች መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም ወላጅ የራሱን ግዴታ ሊወጣ ይገባል። ከዚያ ባሻገር በብዙ ፈተና ውስጥ አልፈን የምናሳድጋቸውን ልጆች ልፋታችን ከመሬት ወድቆ እንዳይቀርና በዕውቀት የዳበረ አዕምሮ ይዘው የሚያድጉ እንዲሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ባይለያቸው መልካም ነው እያልኩ የዛሬ ጽሑፌን በዚሁ አበቃሁ መልካም ሳምንት።